# የመክሊት መቃብር

To: Dear brother Bedilu
With the love of God
[signature]

ኢዮብ ማሞ

# የመከሊት መቃብር

ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል
ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት
በሕግ የተከለከለ ነው::

Copyright © 2001, by Eyob Mamo
All right reserved.
Reproduction of text in whole or in part without the
written consent by the author is unlawful

Printed In Ethiopia

By
Eyob Mamo

Crusaders Ministries Ethiopia
P.O.BOX 2080 CODE 1110
ADDIS ABABA
ETHIOPIA

## ማውጫ

**መግቢያ**

**ምንጩ:-**
*ወደ እግዚአብሔር መጠጋት. . . . . . . . .* 9

**እንቅስቃሴው:-**
*መንፈሳችንን ማንቃት . . . . . . . . . . . . . .* 19

**ማህተሙ:-**
*በብርሃን ውስጥ መመላለስ . . . . . . . . . .* 27

**መከላከያው:-**
*ሰይጣንን መብለጥ . . . . . . . . . . . . . . .*35

**መልህቁ:-**
*ጸንቶ መቆም . . . . . . . . . . . . . . . .* 45

ይህንን መጽሐፍ

ለወላጆቼ ለፊታ/ ማሞ በሼ እና

ለወ/ሮ ደብሪቱ ኃይሌ

ከታላቅ አክብሮት ጋር አበረክታለሁ

# ምስጋና

ይህን የመክሊት መቃብር የተሰኘውን መጽሐፍ ወደ ህትመት ለማድረስ ታይፕ በማድረግና በእርማት የደገፉኝን ባለቤቴን አዲያም ሰሎሞንን፣ እህት ዲና በላይን፣ እህት ገነት ግርማን፣ ወንድም ቢንያም አዲስንና ወንድም ፍሰሃ ተስፋዬን አመሰግናለሁ::

እንዲሁም መጽሐፉ እንዲታተም በገንዘባቸው የደገፉኝን የክሩሴደርስ ቤተ ክርስቲያን አባሎችና አገልጋዮችን እንዲሁም የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አባሎችን ጌታ ይባርካችሁ እላለሁ::

የመጽሐፉን ሽፋን ውብ በሆነ መልኩ እንዲወጣ ስዕሉን ያበረከተልኝን ወንድም ሰሎሞን ሙሉጌታን አመሰግናለሁ::

ሰው ያደረገን፣ የመክሊታችንም ምንጭ የሆነው እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለዘለአለም የተባረከ ይሁን - አሜን!

# መግቢያ

በብዙ ፀጋ አሸብርቆ የነበረው አዳም ከእግዚአብሔር በሚለይ የኃጢአት ማጥ ውስጥ ተቀብሮ ሳለ፣ ወዴት ነህ የሚል ድምጽ መጣለት (ዘፍ. 3:9):: ከዚህ ጥሪ እንደምንረዳው አዳም ከተመደበለት የበረከት መስመር ወጥቶ እስከፋ ሕይወት ውስጥ እንደነበረ ግልጽ ነው:: በሌላ አባባል አዳም ተሰጥቶት የነበረውን መክሊት ጥሎና ቀብሮ ነበር ማለት ነው:: ዛሬም ይህ ድምጽ ወደ ተለያዩ አገልጋዮች ዘንድ ይላካል:: በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ጥሪ በውስጣቸው እንደ እሳት ይንበለበል የነበሩ፣ ዛሬ ግን በተለያዩ እስራቶች የተተበተቡትንና መክሊታቸውን የቀበሩትን አገልጋዮች እግዚአብሔር ፈልጎ የሚያወጣበትና እንደገና በተሃድሶ የሚያቆምበት ዘመን ነው::

ነገር ግን መክሊት ስንል ምን ማለታችን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን በነበረው ትርጉም፣ መክሊት የሚለው ቃል የመሸጫና የመለወጫ ብቃት ያለውን የወርቅ ወይም የብርን ተመን ያሳያል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጌታ በሰጠው ምሳሌ መሰረት መክሊት የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ እንዲያተርፉበት የሚሰጠውን የጸጋ ስጦታ ያመለክተናል:: ስለዚህም መክሊት አንድ አገልጋይ በአገልግሎት በመትጋት ያተርፍበት ዘንድ ከጌታ የሚሰጠው የጸጋ ስጦታ ነው (ማቴ. 25:14-30):: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጠው ከዚህ ምሳሌ እንደምንማረው፣ ወደ ሌላ አገር በመሄድ ላይ የነበረው ሰው ለአገልጋዮቹ «ለእያንዳንዱ እንደ ዓቅሙ» መክሊት ሰጣቸው:: አቅማቸው ያለው ፈቃደኝነታቸው ላይ መሆኑ ጥርጥር የለውም:: ምክንያቱም ከሶስቱ ሰዎች መካከል ሁለቱ በተሰጣቸው መክሊት ለማትረፍ ጥረው ሲሳካላቸው፣ አንዱ ግን ቀድሞውኑ ሙከራ ለማድረግ ፈቃደኝነት አልነበረውም:: ስለዚህም የተሰጠውን መክሊት በመቅበሩ ምክንያት ያለው እንኳ ሲወሰድበት እንመለከታለን::

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መሰረት እንደ አገልጋዮች መክሊት ሲሰጠን ምርጫችን ሁለት ነው:- 1) በመክሊቱ በትጋት በመጠቀም ማትረፍ፣ 2) መክሊቱን በተለያየ ምክንያት መቅበር:: እነዚህ ሁለት እርምጃዎቻችን የራሳቸው የሆነ ውጤት አላቸው:: በመክሊቱ ያተረፈ አገልጋይ ሌላ መክሊት ይጨመርለታል፣ ለውጤቱም ወሰን አይኖረውም:: ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች መክሊቱን የሚቀብር አገልጋይ ያለውም ይወሰድበታል::

ይህ ያለንበት ዘመን የመጨረሻው ዘመን ነው:: ስለዚህም የክርስቶስን ዳግም መገለጥ የሚጋብዘው ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ በሙላት የመሰበኩ ትንቢት ሊፈጸም ይገባዋል:: ይህም ይፈጸም ዘንድ ግድ ነው:: ቤተ ክርስቲያን በባህልና በዘልማድ አገልግሎት፣ እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ ሰው ሠራሽ መዋቅሮች የተተበተበችበት ዘመን እያለፈ ነውና ጌታ ስሙ ይባረክ:: ጌታ ለሕዝቡ አዲስን አሠራር የሚያስተዋውቅበት ዘመን ነው:: ይህም አዲስ አሠራር፣ ጥንት በሐዋርያት ዘመን የነበረ፣ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ባሳለፈችው የጨለማና የአዘቅት ዘመን የተሰረቀባት መለኮታዊ አሠራር ነው:: ከዘነጋነው ብዙ ስለቆየን እግዚአብሔር እንደ አዲስ ሊያስተዋውቀን ያስፈልጋል::

ለዚህ አሠራሩ ተዘጋጅተናል? ወይስ በተለያዩ ሰበቦች መክሊታችን ተቀብሯል? የት ነው ያለነው? ጌታ በሙላት እንዳይሠራብን ተብትቦ የያዘን ሁኔታ ምንድነው? የተሰጠንን መክሊት እያተረፍንበት ነው ወይስ በተለያዩ

ምክንያቶች ቀብረነዋል? እናስተውል! እኛ ጌታን ለመታዘዝ በሙሉ ልባችን እንነሳ እንጂ እርሱ በእኛ ሊሠራ ያሻውን ማንም ሰውና ምንም ሁኔታ ሊያስቆመው በቂ ኃይል የለውም፡፡ ወደ ጥሪያችን እንመለስ! ጸጋችንን እናንሳ! እግዚአብሔር ይህን ዘመን ወደ ፍጻሜ የሚያመጣውን የመጨረሻ ሥራውን ሊሠራ ተነስቷልና አብረነው እንቁም፡፡

ይህ እንዲሆንና ከጌታ የተቀበልነው መክሊት እንዳይቀበር ማድረግ የሚገቡንንና የማይገቡንን ሁኔታዎች ማወቁ ቀዳሚ ነገር ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ምእራፍ አንድ ውስጥ እንደምንመለከተው፣ ከሁሉ በፊት የመክሊታችን ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ልንጠጋ ያስፈልጋል፡፡ ወደ መጽሐፉ ምእራፍ ሁለት ስንገባ፣ ወደ እግዚአብሔር በመቅረባችን ምክንያት የተነሳሳው መክሊታችን እንቅስቃሴው እንዳይቋረጥ መንፈሳችንን ማንቃት እንደሚገባን ያስተምረናል፡፡ በምእራፍ ሶስት ውስጥ እንደምናጠናው፣ ይህ መንቀሳቀስ የጀመረው መክሊታችን እውነተኛነቱና ጤናማነቱ የሚታይበት ማህተም አለ፣ እሱም በብርሃን ውስጥ መመላለስ ነው፡፡ ይህ መክሊት የምንለው መንፈሳዊ ጸጋ ካለማቋረጥ ሊጠበቅ ይገባዋል፡፡ ስለዚህም ሁኔታ በሚገባ ለማጥናት ወደ ምእራፍ አራት እንገባለን፡፡ ከዚህም ምእራፍ እንደምንማረው መክሊታችንን ከጠላት ለመጠበቅ ዋነኛ መከላከያው ሰይጣንን መብለጥ ነው፡፡ የዚህ መጽሐፍ የመጨረሻው ወይም አምስተኛው መእራፍ ይህንን በውስጣችን የተገለጠውን ጸጋ አጽንተን የምንይዝበትን እውነት ያሳየናል፡፡ ከዚህም ምእራፍ እንደምንረዳው፣ በተሰጠን መክሊት ሳንደክምና በታማኝነት እንድናተርፍ የሚረዳን አንድ መልህቅ አለ፣ እሱም ፀንቶ መቆም ነው፡፡

*«እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ» (ራዕ. 2:5)፡፡*

*በዚህ የመጽሐፋችን የመጀመሪያ ምእራፍ ውስጥ የመክሊታችን ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር እንዳንጠጋ የሚያደርጉንን ሁኔታዎች ምን እንደሆኑና፣ እነዚህንም ሁኔታዎች እግዚአብሔር እንደሚመረምር እናጠናለን፡፡ የሚከተሉትን ወደ እርሱ እንዳንቀርብ የሚያደርጉንን ሁኔታዎች እግዚአብሔር ይመረምራል፡፡*

*1) እግዚአብሔርን የማያውቁትን፡፡*

*እግዚአብሔርን የሚያውቁትን የሚከተሉት ምልክቶች ይከተሏቸዋል፡፡*
*ሀ) ሕጉን የሚያስላስሉ ናቸው፡፡*
*ለ) ሁሉን እንደከንቱ የቆጠሩ ናቸው፡፡*
*ሐ) የበረቱ ናቸው፡፡*

*2) ጣዖት ያቆሙትን፡፡*

*የሚከተሉትን ሃሳቦች ቃሉ ከጣዖት ጋር አጣምሮ ጠቅሷቸዋል፡፡*
*ሀ) እልህ (ሃሳበ ግትርነት)፡፡*
*ለ) መጎምጀት፡፡*
*ሐ) ትምክህት፡፡*

*3) ቅን አለመሆንን፡፡*

*በሚከተሉት በረከቶች «የቅኖች ትውልድ ትባረካለች» (መዝ. 112:2)፡፡*
*ሀ) ደስታ፡፡*
*ለ) ምሪት፡፡*
*ሐ) የጸሎት መልስ፡፡*

*4) በለብታ ሕይወት መደላደልን፡፡*

*የሚከተሉት አመለካከቶች ወደዚህ አይነት ሕይወት ውስጥ ይጥሉናል፡፡*
*ሀ) ለሠራናቸው ኃጢአቶች እስካሁን አለመቀጣታችንን ለመድነው?*
*ለ) በቤቱ ውስጥ የሰለጠነን ሥጋዊነት ጌታ አይቀጣም ብለን ደመደምን?*
*ሐ) ጌታ ለእርሱ ብቻ ብለን ያሳየናቸውን ትጋቶች ችላ ያለ መሰለን?*

*5) ክፉ ምኞትን፡፡*

*ከክፉ ምኞት ነጻ ለመሆን የሚከተሉትን እርምጃዎች ልንወስድ ይገባል፡፡*
*ሀ) አሮጌውን ሰው መግደል፡፡*
*ለ) ክፉ ምኞትን መሸሽ፡፡*
*ሐ) እግዚአብሔርን እንደሚገባ ማክበር፡፡*

# 1
# ምንጩ
## *ወደ እግዚአብሔር መጠጋት*

*«እግዚአብሔር ልቡናንና ኩላሊትን ይመረምራል» (መዝ. 7:9)::*

ከጌታ አንዳችም የተደበቀ ነገር የለም:: በዓለም ያለው ሁኔታ ሁሉ በፊቱ ግልጽ ነው:: እግዚአብሔር ሁሉን ያያል፣ ይመረምራልም:: በአንደበቱም ሆነ በሁኔታው ጌታን ሊያታልለው የሚችል ሰው የለም:: እርሱ የልብን አሳብ የሚያውቅ አምላክ ነው::

ምናልባት በዚህ ዘመን በጌታ ቤት ውስጥ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ወደ አገልግሎት የተሰማሩ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም እንኳ፣ ጌታ ግን የእርሱ የሆኑትን የሚያውቅ፣ በልባቸው ንጽህናም የሚሄዱትን ሁሉ የሚያይ አምላክ ነው:: በቤቱ ውስጥ በአገልግሎት የተሰማሩትን አገልጋዮች የውስጥ አሳብ መርምሮ ያውቃል:: ማን ለምን እንደቆመ ይመረምራል:: ይህን እውነት የተገነዘበው የጌታ ባሪያ ዳዊት እንዲህ ሲል ጸለየ:- *«አቤቱ መረመርከኝ አወቅከኝም:: አንተ መቀመጤንና መነሳቴን አወቅህ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ» (መዝ. 139:1-2)::* የዕብራውያን ጸሐፊም ይህንኑ እውነት ያጠናክርልናል:- *«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም፣ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፣ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» (ዕብ 4:12-13)::*

እንግዲህ በውስጣችን ያለው የማንኛውም መልካም ነገርና ተግተን ልናተርፍበት የሚገባን የመክሊታችን ምንጩ እግዚአብሔር ስለሆነ፣ አጥብቀን ወደ እርሱ ልንጠጋ ይገባናል:: ወደ እርሱ በተጠጋን መጠን መክሊታችን እየበዛና እየተትረፈረፈ ይሄዳል:: ከእርሱ በራቅን መጠን ግን መክሊታችን ወደ መዳፈንና ወደ መቀበር ይሄዳል፤ መጨረሻውም የመክሊት መወሰድና ለሚያተርፉ ሰዎች መሰጠት ነው:: ጌታ በእውነት የመልካም ነገር ሁሉ ምንጩ እሱ እንደሆነ በማወቅ ወደ እሱ የቀረቡትን መርምሮ የሚያውቅ አምላክ መሆኑን እንዘንጋ:: ከዚህ በመቀጠል የተጠቀሱት ነጥቦች እግዚአብሔር የሚመረምራቸውን የመክሊት ጸሮች በጥቂቱ የሚያሳዩ ናቸው::

### *1) እግዚአብሔርን የማያውቁትን*

*«እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ይመረምራልና፣ የነፍስንም አሳብ ሁሉ ያውቃልና የአባትህን አምላክ እወቅ» (1ዜና. 28:9)::*

ይህ ንጉሥ ዳዊት በጊዜው በአገልግሎት እንጭጭ ለነበረው ለልጁ ለሰሎሞን የመከረው አስፈላጊ ምክር ነው:: እግዚአብሔር በእውነት የሚያውቁትንና የማያውቁትን ለመለየት ልብን ይመረምራልና እወቀው ብሎ ሲመክረው እናነባለን:: ከዚህም አባባል እንደምንረዳው ሰዎች እግዚአብሔርን ሳያውቁት ሊያገለግሉት እንደሚችሉ ነው:: ምንም እንኳን ጌታን ሳያውቁት



የሚያገለግሉት ለጊዜው በተግባራቸው ቢጸኑም ይህንን ሁኔታ ግን ጌታ ይመረምራል:: አዎ፣ ጌታ ልብን ይመረምራል፤ በእውነትም እርሱን አውቀው የሚያገለግሉትን ለይቶ ያውቃል:: ጌታም ሕዝቡን ሊጎበኝ ሲነሳ፣ የማያውቁት ባሉበት ሲቀሩ፣ እርሱን ለማወቅ የተጉት ግን ፈተናውን በማለፍ ከቅባት ወደ ቅባት ይሸጋገራሉ::

አንድ ክርስቲያን ምንም እንኳ ለአገልግሎት ተጠርቼአለሁ፣ ጌታንም ለማገልገል ራሴን ሰጥቻለሁ ቢል፣ ክርስቶስን በሚገባ ካላወቀ ጸጋው በሙላት ሊገለጥ አይችልም:: ብዙዎች ሳያውቁት ጌታን ያገለግሉታል:: ስለዚህም፣ «አገልጋይ ሆኖ እንዴት . . .?» የሚያሰኙ ጌታን የማያስከብሩ ባህርያት ይታዩባቸዋል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ቤቱን የሚያጠራበት ጊዜ ደርሷል:: ስለዚህም ደግሞ ጌታ ሕዝቡን በሚጎበኝበት ቀን የበረከቱ ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ዛሬ እርሱን የማያውቁት እርሱን ወደማወቅ ይመጡ ዘንድ ጥሪ ያደርጋል:: ይህንንም ጥሪ ሰምተን እግዚአብሔርን ለማወቅ በፈለግነው መጠን እናውቀዋለን፣ ጌታም ራሱን ይገልጥልናል::

ለመሆኑ እግዚአብሔርን የማወቃችን መመዘኛው ምንድነው? እግዚአብሔርን የማወቅ ምስጢር በሕይወታቸው የተለማመዱ ሰዎች ከሚታዩባቸው ምልክቶች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

*ሀ) ሕጉን የሚያሰላስሉ ናቸው::* እግዚአብሔርን ያለማወቅ ዋነኛ ምልክቱ ቃሉን አለማሰላሰልና አለማክበር ነው:: ሕጉ (ቃሉ) በልቦናቸው የተጻፈና የኖረ አገልጋዮች ውጤታማዎችና የሚያደርጉትን የሚያውቁ አገልጋዮች ናቸው:: *«ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፣ ይላል እግዚአብሔር:: ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል:: እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፣ እያንዳንዱም ወንድሙን:- እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና፣ ይላል እግዚአብሔር» (ኤር. 31:33-34)::*

ይህንኑ የብሉይ ኪዳን እውነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ዮሐንስ ልንረዳው በምንችለውና ጥርት ባለ ሁኔታ አስቀምጦታል:- *«ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን:: አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም» (1ዮሐ. 2:3-4)::*

አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮች በዘመን አመጣሽ ጎርፎች ሲወሰዱ ማየት ልብን ያሳዝናል:: በየዕለቱ በሚነሱ የክርስቶስን ትምህርት በሚቃረኑ ሕብረተሰባዊ ለውጦች የሚወሰዱ አገልጋዮች ክርስቶስን አለማወቃቸውን ያስመሰክራሉ:: ጌታን በማገልገል ለአመታት መቆየታችን ክርስቶስን እንደሚገባ የማወቃችን ምልክት ሊሆን አይችልም:: አንዳንድ ሰዎች ለመገለጥ እድል እስኪያገኝ ድረስ በውስጣቸው የተደበቀ የዘረኝነት ስሜት አለባቸው:: ሌሎች የዓለማዊነትን፣ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ የፍልስፍና አስተሳሰቦችን በውስጣቸው አምቀው ሲመላለሱ ይኖራሉ:: የተለያዩ የባህል፣ የአመለካከትና የፍልስፍና ለውጦች ሕብረተሰቡን ሊያናውጡ በሚነሱበት ዘመን ሁኔታው የእነዚህን ክርስቶስን በሚገባ ያላወቁና ያልተለወጡ አገልጋዮች ማንነት አብሮ ይገልጠዋል:: ቀድሞ ያልታየባቸውን ዘረኝነት፣ ቀድሞ ከአንደበታቸው ያልወጣን ቋንቋ፣ ቀድሞ ከእነርሱ ዘንድ ይፈልቃል ተብሎ ያልተገመተን አመለካከት በድፍረት ሲያንጸባርቁ ይገኛሉ:: ክርስቶስን በሚገባ

ቢያውቁት ኖሮ በተለወጡ ነበር። ጌታን ያወቀ አገልጋይ ዘመኑን የሚዋጅ እንጂ በዘመኑ የሚወሰድ አገልጋይ አይደለም። *«ዘመኑን ዋጁ» (ኤፌ. 5:16)*።

*ለ) ሁሉን እንደከንቱ የቆጠሩ ናቸው።* እንደ ክርስቶስ ያለ ማራኪ ውበት ያለው ሰውም ሆነ አምላክ ታይቶ አይታወቅም። ሰዎች ክርስቶስን በሚገባ ሲያውቁት ይህ ውበቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይማርካቸዋል። ስለዚህም ማንንም ሰው ሆነ ምንንም ሁኔታ ከእርሱ ጋር ማወዳደር ስለማይችሉ ሁሉን እንደከንቱ ይቆጥራሉ። *«አዎን፣ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ ስለእርሱ ሁሉን ተጎዳሁ፣ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፣ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፣ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደጉድፍ እቆጥራለሁ እሱንና የትንሳኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታንም ትንሳኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ» (ፊል. 3:8-11)*።

ለእግዚአብሔር መስጠታችንን የሚቀናቀን ሁኔታ ምን አለ? ከእኛና ከጌታ መካከል እየገባ በሙላት እንዳናገለግለው እንቅፋት የሆነብን ጉዳይ አለ? ዓይናችንን እየማረከ፣ ልባችንን ደግሞ እየሳበ ጌታን እንድንዘነጋ የሚያደርገን ሁኔታ አለ? እናስተውል፣ ጌታ ኢየሱስ ከሁሉ በላይ ነው። እርሱ ይበቃናል፣ የቀረው ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው። *«ከንቱ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ፤ ሁሉ ከንቱ ነው» (መክ. 1:2)*።

*ሐ) የበረቱ ናቸው።* አገልጋይ ዘወትር በመቀዘምና በድካም እንዲመላለስ የጌታ ፈቃድ አይደለም። ዘወትር በድካም የሚመላለስ ሕይወት ጌታን በሚገባ ያላወቀ ህይወት ነው። በጸሎትና በቃሉ የማይተጋ አገልጋይ ለክርስቶስ ያለውን እውቀት ውስንነት ያሳያል። የክርስቶስን ውበት የተረዳና ያወቀ አገልጋይ ከእርሱ ጋር ጊዜ አሳልፎ አይጠግብም። በግሉ ከቃሉ ጋር፣ በጓዳው ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕብረት ለማድረግ የማያልቅ ጥማትና ጉልበት ይታይበታል። ራሱንም ለዚህ ትጋት ስላስለመደ ከጌታው ጋር በሚገባ ያላሳለፈ ዕለት ያንን ሕብረት ይናፍቃል። *«ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፣ ያደርጋሉም» (ዳን. 11:32)*።

መቼ ነው የምንበረታው? አምናም ደካሞች ከነበርን፣ ዘንድሮም ደካሞች ከሆንን፣ ለሚመጣውም አመት ደግሞ ብርታትን የሚያንጸባርቅ ዕቅድ ከሌለን፣ መቼ ነው የምንበረታው? ጌታ ለብርታት እንጂ ለድካም አልጠራንም፤ ለድል እንጂ ለመሸነፍ አልጠራንም። በሕይወታችን ካለማቋረጥ ውጊያ መኖሩ መንገዳችንን ከጌታ ጋር እያደረግን ስለመሆኑ ምልክት ሲሆን፣ በመሸነፍና በማጉረምረም መመላለሳችን ግን በጌታ የሚገኘውን የአሸናፊነት ሕይወት የሚያሳይ አይደለምና በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እንነሳ። አምላካችንን እንወቅ፣ እንበርታም። *«አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፣ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፣ አይታክትም፣ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፣ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል ጎበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፤ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፣ እንደንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ አይደክሙም» (ኢሳ. 40:28-31)*።



### *2) ጣዖት ያቆሙትን*

*«የአምላካችንን ስም ረስተንስ ቢሆን እጃችንንም ወደሌላ አምላክ አንስተንስ ቢሆን፣ እግዚአብሔር ይህንን አይመረምርም ነበርን? እርሱ ልብ የሰወረውን ያውቃልና» (መዝ. 44: 20-21)*።

ከውጭ የማይታዩ ውስጣዊ የሆኑ ጣኦቶችን እግዚአብሔር እንደሚመረምር ዳዊት ያስታውሰናል። እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው። እርሱ ብቻ መመለክና መከበርን ይፈልጋል። ለዚህ ነው ሰዎችን ከተለያዩ እስራቶች እየፈታ የእርሱ የግል ንብረት የሚያደርገው። በአጭሩ፣ ሰዎች ለማንኛውም ነገር ተገዢ እንዲሆኑ የጌታ ፈቃድ አይደለም። በተለይም ደግሞ በደሙ የተዋጁና የልዑል አምላክ ባሪያዎች ለመሆን ራሳቸውን የለዩ አገልጋዮቹ ከማንኛውም ዓይነት የጣዖት አሠራር ራሳቸውን ይለዩ ዘንድ ግድ ነው። *«ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና» (1ጴጥ. 4:3)*።

ወደ ክርስቶስ ከመጣንና እርሱን ጌታችን ነው ብለን ልቦናችንን ከከፈትንለት በኋላ ከማናቸውም ዓይነት ጣኦት ራሳችንን ልንለይ ተጠርተናል። ስለዚህም በሕይወታችን ሊኖሩ የሚችሉትን ጣኦቶች መርምረን በመለየት ል[illegible]ራቸው ይገባል። ለመሆኑ ጣዖት እንዳለብን በምን ማወቅ እንችላለን? መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ሶስት ሃሳቦች ከጣዖት ጋር አጣምሮ ያሳየናል።

*ሀ) እልህ (ሃሳበ ግትርነት)።* በልቡ እልከኝነትና ሃሳበ ግትርነት ያለበት ሰው ራሱን እንዲመረምርና ከጣዖት ንስሃ እንዲገባ ይመከራል። እልህና አገልግሎት አብረው አይሄዱም። ነጥቡ እዚህ ላይ ነው፡- እልከኝነትና ሃሳበ ግትርነትን ይዘን ጌታን ማገልገል እንችላለን። ነገር ግን ጌታ ወደ መንግስቱ ሲጠራን ወደ አቀደልን የበረከት ሙላት በፍጹም አንደርስም። ጸጋችን (መክሊታችን) ይቀበራል። ሌሎች ከሙላት ወደሙላት፣ ከቅባት ደግሞ ወደ ቅባት ሲሸጋገሩ እኛ ግን ከዓመት እስከ ዓመት ባለንበት እንረግጣለን። *«እልከኝነትም ጣኦትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው» (1ኛ ሳሙ. 15:23)*።

*ለ) መጎምጀት።* መጎምጀት ወይም ክፉ ምኞት ጣኦትን ከማምለክ ጋር ተጣምሮ እናገኘዋለን። አንድ ሰው በውስጡ ካለው መጎምጀት የተነሳ ስለ ክርስቶስ ለማሰብ ሲሳነው ራሱን ለጣኦት አጋለጠ ማለት ነው። ይህንንም ሁኔታ ጌታ በሚገባ ይመረምራል። በውስጡ የሚመጣበትን ክፉ ምኞትና መጎምጀት ጊዜ ባለመስጠት የሚቋቋም አገልጋይ ይህንን ፈተና የሚያልፍ አገልጋይ ነው። ወደ እርሱ የሚመጣለትን ክፉ ሃሳብ ሁሉ የሚያስተናግድ አገልጋይ ከእስራት ወደእስራት ያዘቅጣል። *«ጣዖትን ማምለክ የሆነ መጎምጀት» (ቆላ. 3:5)* መክሊትን የመቅበር ኃይል አለውና፣ ከማናቸውም ዓይነት መጎምጀትና ክፉ ምኞት ሕዝቡ ነጻ እንዲወጣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በመጎምጀት ሃሳብ የሚባክን አእምሮ በሙላት ለእግዚአብሔር ክብር ሊቆም አይችለውም። በአገልግሎቱ ውስንነት ይሰማዋል። ስለዚህም ማንኛውም አገልጋይ በሙላት ጌታን ማስከበር ከፈለገ ከዚህ እስራት በደሙ ኃይል ነጻ ሊወጣ ያስፈልገዋል። *«የሚመኝ እርሱም ጣኦትን የሚያመልክ» (ኤፌ. 5:5)* መክሊቱን የቀበረ አገልጋይ ነው።

*ሐ) ትምክህት።* ሌላኛው ጣኦትን የሚወክል ቃል ትምክህት ነው። የምንመካበት ማንኛውም ከጌታ ውጭ የሆነ ነገር በጌታና በእኛ መካከል ስለሚቆም

በዚህ የመጽሐፋችን የሁለተኛ ምእራፍ ውስጥ መክሊታችን እንዳይቀበርና እንቅስቃሴው እንዳይገታ መንፈሳችንን ማንቃት እንዳለብን እናጠናለን:: ስለዚህም፣ ከነቃ ሕይወት ወደ እንቅልፍ አሽቀንጥረው የሚጥሉንን ሁኔታዎች እንመለከታለን::

1) አካልን በሥራ ማዛል::

የሚከተሉትን ሁኔታዎች ለማሟላት ሰው ካለማቋረጥ ይደክማል::

ሀ) መጠለያ::

ለ) ትዳር::

ሐ) ወገን::

2) ዓላማ የለሽ ውተታ::

የሚከተሉት አመለካከቶች ሰውን ወደ ዓላማ ቢስነት ይከቱታል::

ሀ) ጊዜ አልፎብኛል ብሎ ማሰብ::

ለ) ራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደር::

ሐ) በመንታ አሳብ ማነከስ::

3) ታካችነት::

ከታካችነት ለመዳን የሚከተሉትን መንፈሳዊ ሕጎች አንዘንጋ::

ሀ) በጥቂቱ የመጀመር ሕግ::

ለ) የማጨድ ሕግ::

ሐ) የመጽናት ሕግ::

4) ረዘም ያለ ደጅ ጥናት::

የመጠበቅ ብዛት እንዳያዝለን የሚከተሉትን በማድረግ እንትጋ::

ሀ) በጸሎት መትጋት::

ለ) በቃሉ መትጋት::

ሐ) ወቅትን በመለየት መትጋት::

5) ጠሊቅ ኀዘን::

የሚከተሉት ሁኔታዎች ጠሊቅ ኃዘን ውስጥ ይከታሉ::

ሀ) እንደጌታ ፈቃድ ያልመጣ «በረከት»::

ለ) ተስፋ ቢስ መሆን::

ሐ) የምንሰማው ነገር::

የናቋቸውን ያከብራል፤ የተረሱትን ያስታውሳል፤ ሰዎች ከቡድናቸው ገፍትረው ያስወጧቸውን ደግሞ በፍቅር ገመድ ስቦ ወዳጅ ያደርጋል:: እርሱ ልዩ ወዳጅ ነው፣ እንደ ሰው አይደለም! አይናችንን በእርሱ ላይ ብቻ እንትከል፣ ያልጠበቅነውን ተአምራት እናያለን:: ምድራዊ ወገን አስፈላጊና ልንመኘው የሚገባን በረከት ነው:: ሆኖም አንድን እውነት አንዘንጋ:- *«ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው አንዳች ሊቀበል አይችልም» (ዮሐ. 3:27)::*

## *2) ዓላማ የለሽ ውተታ*

*«በእውነት ወደ ቤቴ ድንኳን አልገባም፣ ወደ ምንጣፌም አልጋ አልወጣም፣ ለአይኖቼም መኝታ ለሽፋሽፍቶቼም እንቅልፍ፣ ለጉንጮቼም እረፍትን አልሰጥም፣ ለእግዚአብሔር ስፍራ፣ ለያዕቆብም አምላክ ማደሪያ እስካገኝ ድረስ (መዝ. 132:3-5)::*

ዳዊት ራሱን ለእንቅልፍ አሳልፎ እንዳይሰጥ አጽንቶ የያዘው አንድ ዓላማ ነበረው:: ይህም ዓላማው ለእግዚአብሔር ቤትን *መሥራት* ነበር:: በዓላማና በራእይ መሞላት ትጋትን ያጎናጽፋል:: በሕይወታችን ዓላማ በማይኖረን ጊዜና በውስጣችን የሚቃጠል ራእይ በሚጠፋ ጊዜ ለእንቅልፍ ታልፈን እንሰጣለን:: ይህን እውነት ጠቢቡ ሰሎሞን፣ «ተግባር መፍታት እንቅልፍን *ታመጣለች*» (ምሳ. 19:15) ሲል ያረጋግጥልናል:: በሕይወታችን አለ የምንለው ዓላማችን ምንድን ነው? ምን ራእይ አለን? ለእግዚአብሔር *መንግሥት* የምንገነባው ነገር አለን? በሕይወታችን እስከሞት ድረስ ልንተጋለት ቆርጠን የተነሳንለት እውነት አለ? እናስተውል፣ ዓላማ ከሌለን የእንቅልፍ መናኸሪያዎች ነን:: ዓላማ ቢስ መሆን ለእንቅልፍ ይዳርጋል ብለን ካመንን፣ አሁን ደግሞ ዓላማ ቢሶች ሆነን እንድንቀር የሚዋጉን ጠንቆች በዝርዝር እንመልከታቸው::

*ሀ) ጊዜ አልፎብኛል ብሎ ማሰብ::* «የዛሬዋ ቀን ለቀሪው ዘመንህ የመጀመሪያዋ ቀን ናት» የሚለው አባባል እውነት ነው:: እምነቱን በጌታ ላይ የጣለ ሰው ጊዜ አለፈብኝ ብሎ መጨነቅ የለበትም:: ከአብርሃም የበለጠ ለነበረው ምኞትና ራእይ ጊዜው ያለፈበት ሰው አልነበረም:: ጌታ ግን አበቃለት በተባለው በአብርሃም ሁኔታ የሌለውን ወደ መኖር የመጥራት ኃይሉን አስመሰከረ:: *«እርሱም ረአብርሃምረ ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው:: ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው እንደ ተባለ፣ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋ ይዞ አመነ:: የመቶ አመትም ሽማግሌ ስለሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፣ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፣ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም» (ሮሜ 4:17-21)::*

ያንተስ ሁኔታ እንዳበቃለት ይሰማሃል? እድሜዬ አልፏል ብለህ ልታደርገው ከምታስበው ነገር ትከለከላለህ? የጤንነትህ፣ የኑሮህና የትምህርትህ ደረጃ ዓላማህን ሁሉ ትተህ ካለእቅድ እንድትኖር እየተፈታተነህ ነው? አይዞህ ተስፋ አለህ ተስፋህ ደግሞ እግዚአብሔር ነው:: እርሱ በሕይወትህ የጎደለውን ይሞላል:: የሌለውን ወደመኖር *ያመጣል*:: ብቻ እመነው::



*ለ) ራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደር::* የውድድር መንፈስ ማስተዋልን የመዘጋት ኃይል አለው:: ከሌሎች ጋር የሚወዳደር ሰው እግዚአብሔር የሰጠውና ያቀደለት ደረጃ አይደርስም:: ዓላማው ከሌሎች የመስተካከል እንጂ ጌታው ያቀደለት ደረጃ የመድረስ ስላልሆነ ውስን ሆኖ ይቀራል:: ለምን ከሌሎች እኩል ለመሆን እየተጣጣርን በሌሎች ችሎታ እንወሰናለን? ጌታ ለእኛ ያቀደልን ከዚያ ልንደርስበት ከምንወዳደርበት ሁኔታ በላይ እንደሆነስ? እንግዲህ ራእያችንን ሌሎች በደረሱበት ደረጃ በመወሰን ጠባብ እናድርገው:: ለጌታ ክፍት እንሁን:: ሌሎች የደረሱበትን ደረጃ እያየን ስለ እነርሱ ጌታን እናመስግን:: እኛም ደግሞ በበኩላችን ራእያችንን በጌታ ሰፋ አድርገን በተሰጠን ጸጋ እንገስግስ እንጂ ዓላማ ቢስ አንሁን:: ጌታም ያግዘናል:: *«ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንዶች ጋር ራሳችንን ልንቆጥር ወይም ራሳችንን ልናስተያይ አንደፍርምና፤ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ፣ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ አያስተውሉም» (2 ቆሮ. 10:12)::*

*ሐ) በመንታ አሳብ ማነከስ::* በመንታ መንገድ ላይ ቆሞ የሚወላውል ሰው ዓላማ ቢስ ሰው ነው:: አንድ አገልጋይ በሁለት አሳቦች መካከል ሆኖ ግራ በመጋባት ማዕበል ከመዋዠቅ ይልቅ በጌታው ፊት ወድቆ ምሪትን ቢቀበል የተሻለ መንገድ ነው:: በሁለት አሳብ መካከል ግራ መጋባት ዓላማ እንዳይኖረን ያደርጋል:: ካለ ዓላማ መጓዝ ስንጀምር ደግሞ *ሥራ ፈቶች* በመሆናችን የእንቅልፍ መንፈስ እንደሚያንዣብብብን እሙን ነው:: ስለዚህ በጌታ ፊት ወድቆና አሳብን አስተካክሎ በአንድ ዓላማ መገስገሻው ጊዜ አሁን ነው:: *«ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው (ያዕ. 1:7-8)::*

## *3) ታካችነት*

*«አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፣ መንገድዋንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን:: አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት መብሏን በበጋ ታሰናዳለች፣ መሮዋንም በመከር ትሰበስባለች:: አንተ ታካች፣ እስከ መቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሳለህ? ጥቂት ትተኛለህ፣ ጥቂት ታንቀላፋለህ፣ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ እንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፣ ችጋርህም ሰይፍ እንደታጠቀ ሰው ይመጣብሃል» (ምሳ. 6:6-11)::*

ታካችነት ሌላ የእንቅልፍ መንስኤ ነው:: ታካችነት ከስንፍና ጋር የተያያዘ ሁኔታ ነው:: «ነገ» ማለትን የሚያበዛ ሰው ታካች መሆኑን ያሳያል:: «ነገ እጸልያለሁ፣ ነገ ቃሉን አነባለሁ፣ ነገ አገለግላለሁ፣ ነገ ትምህርት ቤት እጀምራለሁ . . .» እያለ፣ የታካች ቀጠሮ ማቆሚያ የለውም:: ይህም ሁኔታ ታላቅ እንቅልፍ ውስጥ ይከታል:: ከዚህ ከታካችነት ለመዳን ብዙ ልናስተውላቸው የሚገቡን መንፈሳዊ ሕጎች አሉ:: የሚከተሉት ነጥቦች ልናስታውስ የሚገቡንን ዋና ዋና ሕጎች ያስታውሱናል::

*ሀ) በጥቂቱ የመጀመር ሕግ::* መቶ ደረጃ ያለው ፎቅ ቤት ላይ ለመውጣት የመጀመሪያዋን ደረጃ መርገጥ፣ ከዚያም ሁለተኛዋን፣ ከዚያም ደግሞ ሦስተኛዋን . . . እያልን አንድ በአንድ እርምጃዎችን ካላጠራቀምን የትም አንደርስም:: በተመሳሳይ ሁኔታ መቶ ብር ለማጠራቀም ከፈለግን የመጀመሪያዋን አንድ ሳንቲም ማስቀመጥ መጀመር አለብን:: ይህ እውነት ብንለማመደውም

ባንለማመደውም ሊሻር የማይችል ሕግ ነው። ለመልካም ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ለስንፍናና ለክፋትም የሚሠራ ሕግ ነው። *«ጥቂት ትተኛለህ ጥቂት ታንቀላፋለህ፣ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ እንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፣ ችጋርህም ሰይፍ እንደታጠቀ ሰው ይመጣብሃል» (ምሳ. 6:10-11)።* ከእንቅልፋችን በነቃን ቁጥር፣ ጥቂት ነች እያልን ሌላ አንድ ደቂቃ ጨምረን ስንተኛ፣ በሰዓታት የሚቆጠሩ ብዙ ውጤታማ ልንሆንባቸው የሚገቡን ጊዜአት ይባክናሉ። መፍትሄው አንድ ነው። ጥቂት የምንላት ሁኔታ ተጠራቅማ ልትበዛ እንደምትችል በማመን መልካምን ነገር ለመለማመድና በጥቂቱ ለመጀመር ዛሬ መወሰን ነው።

*ለ) የማጨድ ሕግ።* የዘራውን እንደሚያጭድ በሚገባ የተገነዘበ ሰው ካለመታከት የሚዘራና የሚዘራውንም የሚያውቅ አገልጋይ ነው። ይህንን ሊለወጥ የማይችል ሕግ የዘነጋ አገልጋይ *ሥራ* ፈትና እንቅልፍ ያጠቃው ሰው ነው። ብናምንም ባናምንም፣ የዛሬ ኑሯችንን የወሰነው የትናንት ተግባራችን ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የዛሬ ምርጫችን የነገውን ኑሯችንን የመወሰን ታላቅ ኃይል አለው። ስንፍናን የሚዘራ ድኅነትን ያጭዳል። በሥጋው ኃጢአትን የሚዘራ ከሥጋው መበስበስን ያጭዳል። ይህን እውነት መረዳት ብቻ ሳይሆን ለመለማመድ መወሰን ከብዙ ድካም ያድነናል። *«ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት» (ገላ.6:9)።*

*ሐ) የመጽናት ሕግ።* አገልጋይ የተሰጠው ተስፋ ላይ የሚደርሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስላደረገ ብቻ አይደለም። በዚያ ተግባሩ መጽናት አለበት። ይህም ሊሻር የማይቻል ሕግ ነው። ጌታችንና አምላካችን የጠበቁትን አገልጋዮቹን በፍጹም አሳፍሮ አያውቅም። በጊዜው ይደርስላቸዋል። ከእንቅልፍ ለመዳን ከታካችነት ነጻ መውጣት ያስፈልጋል። ከታካችነት ነጻ ለመውጣት ልንወስዳቸው ከሚገቡን እርምጃዎች አንዱ ደግሞ የጌታን ፈቃድ በማድረግ መጽናት ነው። ይህን ለማድረግ የወሰነ አገልጋይ የነቃና የተጋ አገልጋይ ነው፣ እንቅልፍን ድል በመንሳት ይመላለሳል። *«የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና» (ዕብ. 10:36)።*

## *4) ረዘም ያለ ደጅ ጥናት*

*«ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ» (ማቴ 25:5)።*

መጠበቅ አሰልቺ ነገር ነው። ከመጠበቅ ብዛት የማያንቀላፋ ሰው የለም። ጥቅሱ ከመጠበቅ ብዛት እንቅልፍ ስለያዛቸው ሲናገር፣ «ሁሉም» ነው የሚለው። ልባሞቹም ሰነፎቹም እንዳንቀላፉ እናነባለን። መጽሐፍ ቅዱሳችን ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ ይህን መጠበቅ የሚለውን አሳብ ካለማቋረጥ ከማስታወስ ወደኋላ አይልም። በተለይም በመንፈሳዊ ሕይወቱና በአገልግሎቱ ከጌታ ጋር ተስማምቶ መኖርን የወደደ ሰው በትጋት መጠበቅን መለማመድ ያስፈልገዋል። በመንፈሳዊ ጉዟችን የተለያዩ ሁኔታዎችን አስመልክቶ ከመጠበቅ ብዛት ዝለን እንዳናንቀላፋ በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ካለማቋረጥ ትጋታችንን ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን።

*ሀ) በጸሎት መትጋት።* አንድ ጊዜ ጌታ ሊጸልይ ከሄደበት ስፍራ ወደ ደቀ መዛሙርቱ በተመለሰ ጊዜ ተኝተው አገኛቸው። በዚያን ጊዜ ነበር፣ «ትጉና ጸልዩ»



(ማቴ. 26:41) በማለት አበረታታቸው። ለመጸለይ መትጋት ያስፈልገዋል። እንቅልፍና ጸሎት አይጥና ድመት ናቸው። ዘወትር እንደተደፋፈጡ ይኖራሉ። በጸሎት የተጋ ሰው ጌታን ለመጠበቅ ትጋትን ያገኛል። ከመጸለይ ያንቀላፋ አገልጋይ ከመጠበቅም የሚያንቀላፋ ሰው ነው።

*ለ) በቃሉ መትጋት።* አገልጋይ ካለማቋረጥ ሊተጋበት የሚያስፈልገው ሁለተኛው ጉዳይ ቃሉን የመመገብ ጉዳይ ነው። ይህን ከማድረግ ለአንድ አፍታ እንኳ ያቋረጠ አገልጋይ ለጠላት በርን ይከፍታል። *«ሰዎች ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ» (ማቴ.13፣25)።* ዘሩ የጌታ ቃል ነው። ይህንንም በመልካም የተዘራ ቃል ለማበላሸት ጠላት መንገድ ያገኘው በእንቅልፍ ምክንያት ነው፣ «ሰዎቹ ሲተኙ»። ጠላታችን ሰይጣን በጸሎት የሚተጋን አገልጋይ የመፍራቱን ያህል፣ ለቃሉ የሚተጋንም አገልጋይ እንዲሁ ይፈራል። ስለዚህም በዚያ ሰው ውስጥ የተዘራውን ቃል ለመስረቅ ያ ሰው በተለያዩ ድካሞች እስከሚያንቀላፋ ይጠብቃል። በተለይም ደግሞ ከመጠበቅ ብዛት የዛለንና ያንቀላፋን ሰው ሲያገኝ ይቀልለዋል። የጌታ ቃል በሙላት ይኖርብን ዘንድ ካለማቋረጥ መትጋት በጠላት አሠራር ላይ ኃይለኛ ብርሃን ያበራበታል፣ ተንኮሉም ይከሽፋል።

*ሐ) ወቅትን በመለየት መትጋት።* የወቅትንና የአዝመራን ግንኙነት የማያውቅ ሰው መቼ መዝራትና መቼ ማጨድ እንዳለበት ስለማያውቅ *መሥራት* በሚገባው ሰዓት ያንቀላፋል። ይህን ምስጢር የተገነዘበ ሰው ግን መቼ *መሥራት*ና መቼ መተኛት እንዳለበት ያውቃል። *«በበጋ የሚያከማች ልጅ አስተዋይ ነው፤ በመከር የሚተኛ ግን እርሱ ራሱን ያስነውራል» (ምሳ. 10:5)።* በተመሳሳይ ሁኔታ የዘመኑን ሁኔታ በመንፈስ የማይመረምር አገልጋይ የጠላትን አሠራር ስለማይለይ ለውጊያ ሲነሳ ሲገባው ሲያንቀላፋ ራሱን ያገኘዋል። በተለይም በመንፈሳዊ ውጊያ ውጤታማ ለመሆን፣ ዘመኑን መለየት እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። እንግዲህ *መሥራት* የማይቻልበት ወቅት ይመጣልና፣ እንቅልፍን ትተን *መሥራት* በምንችልበት በዚህ ዘመናችን ለአምላካችን ክብር እንሩጥለት።

## *5) ጠሊቅ ኀዘን*

*«ከጸሎትም ተነስቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣና ከኀዘን የተነሣ ተኝተው ሲያገኛቸው ስለ ምን ትተኛላችሁ? . . . አላቸው» (ሉቃ. 22:45)።*

ሰው በሕይወት ዘመኑ የተለያዩ ሁኔታዎችን ያሳልፋል። የደስታ ዘመን እንዳለው ሁሉ የኀዘንም ዘመን አለው። በአገልጋይ ሕይወት ሊመጣ ስለሚችለው ኀዘን ያነሳን እንደሆነ ግን አንድ ልናስታውሰው የሚገባን ጉዳይ አለ። ይህም ጉዳይ ኀዘኑ የመጣበትን ምክንያት ለይቶ የማወቅ ሁኔታ ነው። ሁኔታውን እንደ ጌታ ቃል የተመለከትነው እንደሆነ፣ ሁለት የኀዘን ዓይነቶች እንዳሉ እንማራለን። የመጀመሪያው፣ «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን» ነው (2ቆሮ. 7:10)። ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ከሚያመጣቸው መልካም ነገሮች አንዱ «ትጋት» ነው (ቁ.11)። ከጌታ ያልሆነ ኀዘን ግን ውጤቱ ያማረ አይደለም። እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱን ለእንቅልፍ የዳረጋቸው የኀዘን ዓይነት የዓለም ኀዘን እንደሆነ እናስተውላለን። ለመሆኑ ለዚህ ለእንቅልፍ አሳልፎ ወደሚሰጥ የዓለም ኀዘን የሚዳርጉን ጠንቆች ምንድን ናቸው? የሚከተሉት ነጥቦች እንመልከት።

*ሀ) እንደጌታ ፈቃድ ያልመጣ «በረከት»::* አገልጋይ ጌታውን ሳያማክር በራሱ ጥበብ የተለያዩ በረከቶችን ለማግኘት ሲሯሯጥ ኃዘንን ወደ እርሱ ይጠራል:: በዚህም ጥረቱ የተመኘውን ነገር ሊያገኝ ይችላል፣ መጨረሻው ግን ስለማያምር ኃዘንን ያስከትላል:: ጌታን ሳያማክሩ በትዳር መባረክ የፈለጉ አገልጋዮች የተመኘ-ትን ሰው ያገባሉ፣ ብዙም ሳይቆይ ኑሮ ምስቅልቅል ይልና ደስታ በኀዘን ይተካል:: ከጌታ ቃል ውጭ በሆነ መንገድ የንብረት ማከማቸት ተግባር ውስጥ የተሰማሩ አገልጋዮች ለጊዜው የተመኙትን ሊያገኙና ደስ ሊሰኙ ይችላሉ ነገር ግን ጉዳዩ ውስጥ ጌታ ስላልገባበት ኃዘንን ማስከተሉ አይቀርም:: ስለዚህም፣ ኃዘንን ያልጨመረ በረከት የሚፈልግ የእግዚአብሔር ሰው ጌታውን ሳያማክር አንዳች ነገር ውስጥ እንዳይገባ ይቁረጥ:: *«የእግዚአብሔር በረከት ባለጠጋ ታደርጋለች፣ ኃዘንንም ከእርሷ ጋር አይጨምርም» (ምሳ. 10:22)::*

*ለ) ተስፋ ቢስ መሆን::* ሰው ካለምግብና ካለመጠጥ እንዲሁም ካለመጠለያ የተወሰኑ ጊዜአት መቆየት ይችላል:: ተስፋ ከሌለው ግን አንዲትም ደቂቃ መቆም ይሳነዋል:: ተስፋ እየቆረጡ የሄዱ ሰዎች ኃዘን የሞላባቸው ሰዎች ናቸው:: *«ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፣ ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች እንዳታዝኑ» (1ተሰ. 4:13)::* ውስጡ አሳርፍ ያለው፤ ከእንቅልፉ በፊት ያለው የመጨረሻ አሳቡ የሚያስጨንቅ፣ ጠዋት ሲነቃ ደግሞ መጀመሪያ ወደ ሕሊናው የሚመጣው አሳብ የሚረብሽ እየሆነ የተቸገረ አገልጋይ ራሱን ይመርምር:: አንዳችም ተስፋ የቆረጠበት ሁኔታ ካለ ለጌታው ያስረክብና ይረፍ፣ ነጻነቱንም ያውጅ:: ኢየሱስ ተስፋችን ነው:: ስለዚህም ተስፋ መቁረጥ በስሙ ሊነቀል ይገባዋል:: ተስፋ መቁረጥ እስካለ ድረስ ኀዘን አለ:: ኀዘን ካለ ደግሞ የነቃና የተጋ ሕይወት መምራት አይቻልም::

*ሐ) የምንሰማው ነገር::* ሰው በሚሰማው ነገር እንደሚወሰድ ማብራሪያ የማያስፈልገው እውነት ነው:: «እምነት ከመስማት ነው» የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የሚሠራው ለጌታ ቃል ብቻ አይደለም:: አለ የተባለ ፍልስፍና፣ ሃይማኖትም ሆነ የቀለም ትምህርት የሚተላለፈውና ተቀባይነት የሚያገኘው በመናገርና በመስማት ነው:: ይህን እውነት በሚገባ ስናስተውል ሰው የሚሰማው ነገር ወደ ሕይወቱ ኀዘንን ሊያመጣ እንደሚችል እንገነዘባለን:: *«ነገር ግን ይህን ስለ ተናገርኋችሁ ኀዘን በልባችሁ ሞልቷል» (ዮሐ. 16:6)::* አንዳንድ ጊዜ በቀኑ መጨረሻ ወደ ቤታችን ስንገባ የሚሰማንን ደስ የማይል የጭንቀትና ቅር የመሰኘት ስሜት ስንመረምረው ቀን ከሰማነው ነገር ጋር ተያይዞ የምናገኘው ጥቂቶች አይደለንም:: ይህን ከመስማት የሚመጣን ኀዘን ለማሸነፍ የፈለገ አገልጋይ ከጌታው መንፈስ ጋር የተወዳጀ ሕይወት ያስፈልገዋል:: ቃሉንና መንፈስ ቅዱስን የሚያዳምጥ አገልጋይ ዓለም የምታስተጋባውን የኀዘን ጥሪ የማሸነፍ ብርታትን ያገኛል:: ወደ እኛ የሚመጣውን ነገር ከመስማት ራሳችንን ማስወገድ ባንችልም እንኳ፣ በጌታ ቃል ተሞልተን የምንሰማቸው ነገሮች ወደ እኛ በሚያመጡት ኀዘን ላይ ለመጫማት እንችላለን::



*በዚህ የመጽሐፋችን ሰስተኛ ምእራፍ ውስጥ የመከሊታችን ማህተም የሆነውን ቁልፍ እውነት እንመለከታለን:: ይህም እውነት በብርሃን መመላለስ ነው:: ይህ ብርሃን የተሰኘው ሰማያዊ በረከት በሕይወታችን እንዳይነግስ የሚዋጉ የጨለማ አይነቶችን እናጥና::*

1. *የኃጢያት ጨለማ::*
   *የሚከተሉትን የኃጢአት አይነቶች እናጢን::*
   *ሀ) አታድርጉ የተባልነውን ማድረግ::*
   *ለ) በጎ የሆነውን እያወቅን አለማድረግ::*
   *ሐ) የኃጢአት ቀጠሮ መያዝ::*

2. *ምስክር ያለመሆን ጨለማ::*
   *በሚከተሉት ሁኔታዎች በቃልና በስራ ምስክር ለመሆን እንትጋ::*
   *ሀ) አገልግሎትን አስመልክቶ::*
   *ለ) ፍቅርን አስመልክቶ::*
   *ሐ) መልካም ባህሪን አስመልክቶ::*

3. *የክፋት ጨለማ::*
   *በክፉ ላይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ልንወስድ ይገባናል::*
   *ሀ) ክፋውን እንጸየፍ::*
   *ለ) ክፉን በክፉ አንመልስ::*
   *ሐ) በክፉ አንሸነፍ::*

4. *የእንቅልፍ ጨለማ::*
   *እንቅልፍን ለማሸነፍ የሚከተሉትን ነጥቦች እናስታውስ::*
   *ሀ) በመጠን መኖርን እንለማመድ::*
   *ለ) የመጨረሻ ዘመን መሆኑን እናስታውስ::*
   *ሐ) እንደ ብርሃን ልጆች እንመላለስ::*

5. *የጥላቻ ጨለማ::*
   *ጥላቻን በሕይወቱ ያዘለ ሰው በሚከተሉት ስሞች ተጠርቷል::*
   *ሀ) ነፍሰ ገዳይ::*
   *ለ) ሃሰተኛ::*
   *ሐ) እውር::*

# 3

# ማህተሙ

## በብርሃን ውስጥ መመላለስ

*«እንግዲህ የጨለማውን ስራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ:: በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ» (ሮሜ 13:12-13)::*

እግዚአብሔር ብርሃን ነው:: በእርሱ ዘንድ ጨለማ ፈጽሞ የለም:: በልጁ በክርስቶስ አምነው ወደ መንግስቱ የፈለሱ ባሪያዎቹንም ከጨለማ ወደ ብርሃን ያሸጋግራቸዋል:: ነገር ግን ይህ ማለት አንድ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ በኋላ ፈጽሞ ከጨለማ ጋር ለዘለአለም አይገናኝም ማለት አይደለም:: ምርጫው የእያንዳንዱ ሰው ነው:: እንደ ብርሃን ሰው በአግባብ ያልተመላለሰ ክርስቲያን ከጨለማ ስራ ጋር መተባበሩ የማይቀር ነው:: ይህ ደግሞ አደገኛ የሆነ ጸጋን የመቅበር ኃይል አለው::

የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እጅግ ከጎዷት ሁኔታዎች አንዱ በጨለማ የሚመላለሱ አገልጋዮችዋ ጉዳይ ነው:: ጌታ ባጎናጸፋቸው የብርሃን ሕይወት ተሞልተው ስለሚመላለሱት አገልጋዮች ጌታን እንባርካለን:: ነገር ግን ከጌታ በተቀበልነው ሰማያዊ ብርሃን ሳይሆን በደከመ ሕይወት ከጨለማ ጋር ተወዳጅተን ለምንኖር የክርስቶስ ባሪያዎች ጌታ፣ «ወደ ብርሃኔ ተመለሱ» ይለናል:: እንኳን ራሳችንን ለጨለማ አሰራር አጋልጠን ቀርቶ፣ ሙሉ በሙሉ ለጌታ ተሰጥተን እንኳን አገልግሎት ሰልፍ እንደሆነ ግልጥ ነው:: ከጨለማ ጋር ተዳብሎ ቅባት የሞላበት አገልግሎት ለማገልገል ፈጽሞ የማይቻል ነው::

በዚህ ጉዳይ ላይ በጠለቀ ሁኔታ ለማጥናት እንዲመቸን የተወሰኑ ነጥቦችን እስነዝራለሁ:: እነዚህ ነጥቦች የሚያመለክቱን ክርስቲያንን በቀላሉ ሊያጠቁት የሚችሉትን የጨለማ ሕይወት አይነቶች ነው:: አንድ ጊዜ እነዚህን የጨለማ አሰራሮች በጌታ ቃል መንጥረን ካወጣናቸው በኋላ የጌታን ብርሃን እናበራባቸዋለን:: እንደገናም ጌታ ወዳዘጋጀልን የሙላት ሕይወት እንመለሳለን:: ጌታም ቅባቱን በማትረፍረፍ ሊያፈስልን ይጀምራል::

## 1. የኃጢያት ጨለማ

*«ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት:- እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት:: ከእርሱ ጋር ሕብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ሕብረት አለን፣ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል» (1ዮሐ. 1:5-7)::*

ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ እንደሚያብራራልን፣ አንድ ክርስቲያን ከማንኛውም ዓይነነት ኃጢአት ጋር ህብረት በሚያደርግበት ጊዜ ከብርሃን እንደሚለይና በጨለማ እንደሚመላለስ እንረዳለን:: ኃጢአት ማለት ጨለማ ማለት ነው:: ስለዚህም በኃጢአት ውስጥ እየተመላለስን ከጌታ ጋር ህብረት አለን ማለት አስቸጋሪ ጉዳይ ነው:: አንዳንዶቻችን የተለያዩ ኃጢያቶችን እየተለማመድን ለአገልግሎት በመቆማችን ለጊዜው ሁሉ ሰላም ሊመስለን ይችላል:: ነገር ግን በሕይወታችን



ውስጥ የኃጢአት ጨለማ እስካለ ድረስ ሁሉ ሰላም ሊሆን አይችልም:: ለአገልግሎቱ ጌታ ስለ ስሙ ሲል ብቻ የሚሰራውን ድንቅ እየቆጠረ በኃጢያት የመመላለሱን ሁኔታ እያቀለለ ያለ አገልጋይ ትልቅ ስህተት እየሰራ ነው:: ጌታ መሃሪ ነው:: ነገር ግን ጌታ የሚቆጣና የሚጥልም አምላክ ነው:: ቃሉን ሳያጥፍ መሃሪነቱን በታማኝነት እንዳሳየን፣ የሚቀጣ መሆኑንም ቃሉን አክብሮ ያሳየናል:: እንግዲህ እናስተውል:: እኛም እንደ ዳዊት:- *«ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፤ እነርሱ ይምሩኝ» (መዝ. 43:3)* በማለት በንስሃ እንውደቅ:: የሚከተሉትን ነጥቦች ብናስተውላቸው በምን የተለመዱትን የኃጢአት ስህተቶች ያመላክቱናል::

*ሀ) አታድርጉ የተባልነውን ማድረግ::* ቃሉ አታድርጉ ያለንን ነገር በምናደርግበት ጊዜ ኃጢአት እንሰራለን፣ ጨለማም ወደ እኛ ይቀርባል:: የእግዚአብሔርን ቃል እንደተረዳነው መጠን ከኃጢያት ለመቆጠብና አታድርጉ የሚለንን ላለማድረግ ራሳችንን ልናስለምድ ይገባናል:: *«ልጆቼ ሆይ፣ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እፅፍላችኋለሁ» (1ዮሐ. 2:1)::*

*ለ) በጎ የሆነውን እያወቅን አለማድረግ::* ኃጢአት ማለት ክፉ ነገር ማድረግ ብቻ ነው ብለን የኃጢአትን ትርጉም በዚያ ከወሰንነው ተሳስተናል:: በጎ የሆነ ሊደረግ የሚገባው ማንኛውም ነገር ካለና እያወቅን ካላደረግነው፣ አለማድረጋችን ኃጢአት እንደሆነ የጌታ ቃል ያስተምረናል:: ስለዚህም ኃጢአት፣ በማድረግ ብቻ የተወሰነ አይደለም:: ባጭሩ፣ በጎ የማድረግን እድል እንዳላዩ ማለፍ ኃጢአት ነው:: *«እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሰራው ኃጢአት ነው» ( ያዕ. 4:17)::*

*ሐ) የኃጢአት ቀጠሮ መያዝ::* አንዳንድ ጊዜ የሠራነውንና የተፀፀትንበትን ኃጢአት ንስሃ ስንገባ በውስጣችን ያንኑ ኃጢአት ደግመን እንደምናደርገው እናውቀዋለን:: ይህን ሁኔታ፣ «የኃጢአት ቀጠሮ» ብለን ልንሰይመው እንችላለን:: ሁኔታውን ማስወገድ ሲችል፣ ከዚህ በፊት ደግሞ ደጋግሞ የወደቀበት ኃጢያት አካባቢ የሚያንዣብብ ሰውና ራሱን ለዚያው ኃጢአት እንደሚያጋልጥ በውስጡ እያወቀ ንስሃ የሚገባ ሰው ከዚህ ክፍል ይመደባል:: ምህረት የሚገኘው በንስሃ ብቻ ሳይሆን ለመተው በመወሰንም ጭምር ነው:: እናስተውል:- *«ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛል (ምሳ. 28:13)::*

## 2. ምስክር ያለመሆን ጨለማ

*«እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ:: በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም:: መብራትንም አብርተው ከእንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል:: መልካሙን ስራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» (ማቴ. 5:14-16) ::*

በርቶ ከእንቅብ በታች የተደበቀ መብራትና አንደኛው ያልበራ መብራት ልዩነት የላቸውም:: መብራትን የማብራታችን ቁም ነገሩ ለአካባቢው መታየቱ እንጂ እንደው መብራቱ አይደለም:: ጌታ ከጨለማ ወደ ብርሃን ሲጠራን፣ «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ብሎ ነው የጠራን:: ስለዚህም የእርሱ ምስክሮች ስንሆን ብርሃንን እናንጸባርቃለን:: የምስክርነት ሕይወት ሲጠፋ ደግሞ እንደጨለማ ልጆች መመላለስ እንጀምራለን:: ይህን እውነት ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ያጠናክርልናል:- *«እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ*

*ሆተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ጴጥ. 2:9)::* የሚከተሉትን ሦስት ነጥቦች አስመልክቶ ክርስቲያን በቃልም ሆነ በስራ ለምስክርነት ሲውል በብርሃን ውስጥ የመመላለሱ ጉዳይ እውን ይሆናል::

*ሀ) አገልግሎትን አስመልክቶ::* አንዳንድ ጊዜ በአንደበታችን የምናወራለት የክርስቶስ ክብርና ተአምራት በተግባር ስለማይታይ ምስክርነታችን ሙሉ አይሆንም:: ውጤታማ የሆነ የምስክርነት ሕይወት ከፈለግን ግን በአንደበታችን የምንመሰክረው የጌታ ተአምራታዊ ኃይል በተግባር ይገለጽ ዘንድ በጌታ ፊት እንውደቅ:: በአንደበታችን የምንመሰክረው ነገር በተግባር ሲያዩ አሕዛብ ይማረካሉ:: *«አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በስራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእኔ አድርጎ ከሰራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም» (ሮሜ. 15:18-19)::*

*ለ) ፍቅርን አስመልክቶ::* እኛ ክርስቲያኖች የጌታን ተዓምራዊ ኃይል ብቻ አይደለም ልንመሰክር የተጠራነው:: እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑንም አንደበታችን ብቻ ሳይሆን ተግባራችን ሊመሰክር ይገባዋል:: የብርሃን ልጆች መሆናችንን ለዓለም ለማሳየት፣ ፍቅር የመጀመሪያው መሣሪያ እንደሆነ ጌታ አስተምሮናል:: ይህ ፍቅር የተሰኘው ታላቅ የሆነ የመመስከሪያ መሣሪያ ደግሞ ከአንደበት አልፎ በተግባር ሲታይ ወሰን የሌለው ውጤታማነት አለው:: *«ልጆቼ ሆይ፣ በስራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ» (1ዮሐ. 3:18)::*

*ሐ) መልካም ባህሪን አስመልክቶ::* ይህን ነጥብ ለማብራራት *«በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በስራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ» (ሉቃ. 24:19)* መተረኩ በቂ ነው:: ይህ ወደር የማይገኝለት አምላካችን በአንደበቱ ሆነም በባህሪው እንከን አይወጣለትም:: በኃጢአቱ አይደለም የሞተው፤ እርሱ እራሱ በፈቃደኝነት *«ለኃጢአት ሞቷልና» (ሮሜ6:10):: «እርሱም ኃጢአት አላደረገም» (1ጴጥ. 2:22)፣* ነገር ግን እግዚአብሔር ለዓለም ካለው ፍቅሩ የተነሳ *«ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ ኃጢያት አደረገው» (2ቆሮ. 5:21)::* እርሱ አምላክ ስለሆነ ነው ከኃጢአት ነፃ የሆነው እንዳንል፣ *«ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው» (ዕብ. 4:15)::* እንግዲህ ይህንን ክርስቶስን ልንመስል ተጠርተናል::

## *3. የክፋት ጨለማ*

*«ብርሃን ወደ ዓለም ስለመጣ ሰዎችም ስራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው:: ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፣ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፣ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል» (ዮሐ. 3:19-21)::*

በውስጡ ክፉ አሰራር ያለበት ክርስቲያን ከብርሃን ወደ ጨለማ የተመለሰ ሰው ነው:: በክርስቶስ ደም የተዋጀ አገልጋይ ከክፋት ጋር ምንም ሕብረት ሊኖረው አይገባም:: የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን በክፋት ጨለማ ውስጥ በነበሩበት ወቅት በነቢዩ ኢሳይያስ ያመጣላቸው የተግሳፅ ቃል ይህን እውነት የሚያሳይ በመሆኑ እንመልከተው:: *«እኔስ የመረጥኩት ፆም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፣ የቀንበርን ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፣ የተገፉትንስ*



*አርነት ትሰድዱ ዘንድ፣ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን:: እንጀራህንስ ለተራብ ትቆርስ ዘንድ፣ ስደተኞቹን ድሆች ወደቤትህ ታገባ ዘንድ፣ የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፣ ከስጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን:: የዚያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል፣ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል፣ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል፣ የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል» (ኢሳ. 58:6-9)::*

ክፋትን አስመልክቶ ከተወያየን አይቀር ክፉ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ ሊኖረን ስለሚገባው እርምጃ መፅሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረን እውነቶች ዋና ዋናዎቹን ተመልክተን እንለፍ::

*ሀ) ክፉውን እንጸየፍ::* እግዚአብሔር ክፉ የሆነውን ነገር የመጸየፍ ልብን እንዲሰጠን ልንጸልይ ይገባናል:: ክፋት ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለምና የክፋትን መልክ ከያዘ ከማናቸውም ነገሮች ልንሸሽና ልንርቅ ይገባናል:: *«ክፉውን ነገር ተጸየፉት» (ሮሜ. 12:19)::*

*ለ) ክፉን በክፉ አንመልስ::* ሰው በተፈጥሮው መበቀልን ይወዳል:: አንድ ሰው በሚከፋብን ጊዜ እኛም በክፋት ለመበቀል ከተነሳን የዚያ ሰው ድካም ወደ እኛ ዘለለ ማለት ነው:: ስለዚህም ለተደረገብን ክፋት አፀፋ ለመመለስ ከማሰብ መቆጠብ እንለማመድ:: ያን ጊዜ እግዚአብሔር በእውነት ይባርከናል:: *«ለማንም ስለክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ» (ሮሜ.12:17)::*

*ሐ) በክፉ አንሸነፍ::* ክፋት ሲከብበን ከማለቃቀስና ከመደካከም፣ በውስጣችን በሞላው መንፈስ ቅዱስ በመመካት ክፋትን ሁሉ በመልካምነታችን ለማሸነፍ ልንነሳ ያስፈገናል:: ይህ ቀላል የሆነ እርምጃ አይደለም:: ነገር ግን በክርስቶስ የማይቻል ምን አለ? የክፋት መድሃኒቱ በተቃራኒው አቅጣጫ መጓዝ ነው:: ይኸውም መልካምነት ነው:: *«ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ» (ሮሜ. 12:21)::*

## *4. የእንቅልፍ ጨለማ*

*«እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ» (1ተሰ. 5:5-6)::*

የእንቅልፍን መንሥኤዎች አስመልክቶ ሰፋ ባለ ሁኔታ በቀደመው ምዕራፍ ውስጥ ተገልጧል:: ሆኖም፣ በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከተው የእንቅልፍንና የጨለማን ግኑኝነት ስለሆነ ጥቂት ነጥቦችን ሰንዝሬ አልፋለሁ:: በፍጥረታዊው አለም ውስጥ እንቅልፍ ከጨለማ ጋር አብሮ እንደሚታይ ሁሉ፣ በመንፈሳዊውም አለም እንዲሁ ነው:: በቀን ማንቀላፋት አልተለመደምና የሚያንቀላፋ ሰው እንደጨለመበት ያስመሰክራል:: እንግዲህ ከእንቅልፍ ጨለማ ለመዳን የሚከተሉትን ነጥቦች እናስተውላቸው::

*ሀ) በመጠን መኖርን እንለማመድ::* በመጠን አለመኖር ወደ እንቅልፍ እንደሚወስደን ቃሉ ያስተምረናል:: ስላለው ጥቂት ነገር ከማመስገን ይልቅ ዘወትር ሌላን የሚመኝ፣ ጌታ አትረፍርፎ ሰጥቶትም እያለ ሁልጊዜ የማይረካ ከዚህ ክፍል ውስጥ ይመደባል:: ስላለን ነገር ልናመሰግን፣ ስለጎደለን ነገር ደግሞ ለምነን ለመቀበል ተጠርተናልና ከማይረካ ሕይወት እንጠበቅ፣ በመጠንም እንኑር:: «እኛ

*ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ» (1ተሰ. 5:5-6)::*

*ለ) የመጨረሻ ዘመን መሆኑን እናስታውስ::* የጌታን ምጽአት በማሰብ የሚኖር ክርስቲያን የነቃና የተጋ ሰው ነው:: የነገር ሁሉ ፍጻሜ በቀረበበት በዚህ በመጨረሻው ዘመን ሕይወትን የሚያዝል ፍልሚያ ውስጥ ስላለን ከመቸውም የበለጠ ትጋትና ንቃት ይጠበቅብናል:: የመጨረሻው ሰአት ከእንቅልፍ የመነሻ ሰአት ነው:: *«ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰአት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቧልና:: እንግዲህ የጨለማውን ስራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ» (ሮሜ 13:11-12)::*

*ሐ) እንደ ብርሃን ልጆች እንመላለስ::* በጨለማ አሰራር ከተያዙ ሰዎች ተፅዕኖ ለመዳን ካስፈለገ፣ ሁሉን እየመረመርን እንደብርሃን ልጆች ልንመላለስ ይገባናል:: ነገር ግን ባለማስተዋል ከጨለማ ስራቸው ጋር ከተባበርን ከጨለማና ከእንቅልፍ አናመልጥም:: ብዙዎች ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ ተጠምደው አንቀላፍተው፣ ፀጋቸውንም ጥለዋል:: የየእለት እርምጃችን እንደቃሉ የሆነና በብርሃን የታጀበ ሲሆን ሕይወታችን ከእንቅልፍ ይጠበቃል:: *«እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ:: ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፣ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፣ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ስራ ጋር አትተባበሩ፣ ይልቁን ግለጡት እንጂ፣ እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳን ነውር ነውና፤ ሁሉ ግን በብርሃን ሲገለጥ ይታያል፤ የሚታየው ሁሉ ብርሃን ነውና:: ስለዚህ አንተ የምተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሳ ክርስቶስም ያበራልሃል ይላል» (ኤፌ. 5:7-14)::*

## *5. የጥላቻ ጨለማ*

*«በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ አለ:: ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል ማሰናከያም የለበትም፤ ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፣ በጨለማም ይመላለሳል፣ የሚሄድበትንም አያውቅም፣ ጨለማው አይኖችን አሳውሮታልና» (1ዮሐ 2:9-11)::*

በማንኛውም አይነት መልኩ የሚገለጥ ጥላቻ ከእግዚአብሔር አይደለም:: በተለይም ደግሞ በክርስቶስ ደም ተዋጅቶ ከድቅድቅ ጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የተጠራ ወገን በሕይወቱ ከጥላቻ ፈጽሞ ነጻ ሊወጣ ያስፈልገዋል:: የማንኛውም ዓይነት ሰው ሁኔታ በማንኛውም ጊዜ ወደጥላቻ ሊወስደን አይገባም:: ማንም ሰው በልቡ ላለበት የጥላቻ መንፈስ በቂ ምክንያት ሊኖረው አይችልም:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ለመጥላታችን «በቂ ምክንያት» ያለን ይመስለናል:: ነገር ግን በራሳችን አእምሮ በቂ ምክኒያት ነው ብለን ያመንበትን ሁኔታ እግዚአብሔር አይቀበለውም:: ጌታ እኮ እኛን ለመጥላትና ለመተው የሚያበቃ ምክንያት ነበረው:: በምህረቱ ግን ተቀብሎ አቀፈን::

የጥላቻን አስከፊ ገፅታ እንዲህና እንዲያ ብሎ ማንም ሰው ከሚያብራራው በበለጠ ሁኔታ ቃሉ አስቀምጦታል:: እንግዲህ የሚያስፈልገን ይህን ቃል ማንበብና በቁም ነገር መውሰድ ነው:: አንዳንዶቻችን በሰው ያለው ጉድፍ ይታየናል፣ በልባችን ውስጥ ግን ጥላቻ ሞልቷል:: የሰዎችን የውጭ ሁኔታ እየተቃወምን



ከመስበካችን በፊት በልባችን ያለውን ጥላቻ ልናጸዳ ይገባል:: «ትልልቅ» ኃጢያቶች ናቸው ብለን ራሳችን የወሰንናቸውን እነዝሙትንና ስካርን ከመውቀሳችን በፊት ጥላቻን ከውስጣችን እናውጣ::

ጥላቻን እግዚአብሔር ይጠላዋል:: በእርሱ ዘንድ ያለው ፍቅር ብቻ ነውና ጥላቻን ይጸየፋል:: ይህንንም እውነት በመረዳት የእርሱን ስም የሚሸከሙ አገልጋዮች ሁሉ ልባቸውን ከጥላቻ እንዲያጠሩ ጌታ ይፈልጋል:: በልቡ ጥላቻ ያለበትን ሰው ጌታ በተለያየ ዓይነት ስም ጠርቶታል:: የሚከተሉት ነጥቦች ጥላቻ በልባቸው ለነገሰባቸው ሰዎች ጌታ የሰጣቸውን ስሞች ያስታውሰናል::

*ሀ) ነፍሰ ገዳይ:: «ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ» (1ዮሐ. 3:15)::* እናስተውል! ወንድሙን የሚጠላ ሰው እንደ ነፍሰ ገዳይ ሊቆጠር ይችላል አይደለም ቃሉ የሚለው:: ነገር ግን ወንድሙን የሚጠላ ሰው «ነፍሰ ገዳይ ነው» በማለት በግልጽ ነው የሚናገረው:: የዚህን ቃል ትርጉም ለማወቅ ወደ ግሪኩ ጽሁፍ ሄደን መመርመር አያስፈልገንም፣ ግልጽ ነው:: እውነትነቱን መስበክና መለማመድ ብቻ ነው የሚያስፈልገን:: ይባስ ብሎ ጥቅሱ ወንድሙን የሚጠላ ሰው የዘላለም ሕይወት በርሱ የለም ይለናል:: ምን ማለቱ ነው? መልሱ ገልጽ ስለሆነ ለአንባቢዩ እተወዋለሁ::

*ለ) ሃሰተኛ:: «ማንም:- እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን» (1ዮሐ. 4:20-21)::* ከዚህ ክፍል ደግሞ እንደምንማረው ጥላቻ ያለበት ሰው ሃሰተኛ እንደሆነ ነው:: ይህስ ክፍል ማብራሪያ ያስፈልገው ይሆን? ትርጉሙንስ ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መማር ያሻን ይሆን? ለመሆኑ በዘመናችን እርስ በርሳቸው የተጠላሉና በዓለም እንኳ የሚያጸይፍ ሁኔታ እስኪታይባቸው ድረስ የተከፋፋ አገልጋዮችና አብያተ ክርስቲያናት ይኖሩ ይሆን? አሁንም መልሱን ለአንባቢዩ እተወዋለሁ::

*ሐ) እውር:: «ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፣ በጨለማም ይመላለሳል፣ የሚሄድበትንም አያውቅም፣ ጨለማው አይኖቹን አሳውሮታልና» (1ዮሐ. 2:11)::* ይህ ክፍል ደግሞ ጥላቻ ያለበትን ሰው እውር ይለዋል:: ሌሎች እናስተውል፣ እነዚህ መልዕክቶች የተጻፉት ለክርስቲያን ወንድሞች ነው:: ሌሎች ሰዎች በስህተት ሲገኙ የሚሄዱበትን ጎዳና በመቃወም፣ «የምትሄዱበትን አታውቁም» በማለት የሚወቅሳቸው አገልጋይ ከእውርነታቸው ሊመልሳቸው ነውና መልካምን አድርጓል:: ነገር ግን ይህን ተግባራቸውን አይቶ የሚጠላቸው፣ እነርሱ በሌላ መልኩ ይታወሩ እንጂ እርሱም ባለበት ጥላቻ ምክንያት ታውሯል:: በአገልግሎት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ጥላቻ ፈጽሞ ተወግዷል ወይ? የዚንም ጥያቄ መልስ ለአንባብዩ ትቼ አልፋለሁ::

«ብርሃን ጣፋጭ ነው» (መክ. 11:7)::

በዚህ የመጽሐፋችን አራተኛ ምእራፍ ውስጥ መከሊታችንን ከጠላት ለመከላከል የሚያስችሉንን እውነቶች እንማራለን:: ይህም መከላከያ ሰይጣንን መብለጥ ነው:: ስለዚህም ሰይጣን በሕይወታችን እንቅስቃሴ ሲያደርግ የምናውቅባቸውን መመዘኛዎች እንመለከታለን::

1. ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ቅንአት::
   በተለያየ ደረጃ በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ላይ ከመቅናት እንጠበቅ::
   ሀ) በአቻዎቻችን ላይ አንቅና::
   ለ) በብላቴኖች ላይ አንቅና::
   ሐ) በበላዮቻችን ላይ አንቅና::

2. ጥድፊያ የታከለበት ውሳኔ::
   የሚከተሉት ሁኔታዎች የሰይጣን ማዋከብ መጠቀሚያዎች ናቸው::
   ሀ) በሰዎች ግፊት የሚመጣ ውክቢያ::
   ለ) ከሕልም ብዛት የሚመጣ ውክቢያ::
   ሐ) ከሁኔታዎች መለዋወጥ የሚመጣ ውክቢያ::

3. ክስና ፍርድ::
   የሚከተሉት ሰበቦች የክስና የፍፎድ መንስኤዎች ናቸው::
   ሀ. በኃጢአት መቆሸሽ::
   ለ. ከእምነታችን መጠን ያለፈ ዕቅድ::
   ሐ. ስህተት ፈላጊነት::

4. ሽንገላና ውሸት::
   በሚከተሉትን ነጥቦች አስመልክቶ ውሸትንና ሽንገላን እናስወግድ::
   ሀ. ንግግራችንን አስመልክቶ::
   ለ. ፍቅራችንን አስመልክቶ::
   ሐ. እንግዳ መቀበልን አስመልክቶ::

5. ያለመከናወን ችግር::
   ከኋላ ቀርነት ለመዳን በሚከተሉት እንትጋ::
   ሀ. ማድረግ የሚገባንን ለማወቅ በጸሎት መትጋት::
   ለ. ማድረግ የሚገባን ለማስተዋል መትጋት::
   ሐ. ያስተዋልነውን ለማድረግ መትጋት::

# 4

# *መከላከያው*

## *ሰይጣንን መብለጥ*

*«በሰይጣን እንዳንታለል፤የእርሱን አሳብ አንስተውምና» (2ቆሮ. 2:11)::*

ጠላታችን ሰይጣን በክርስቲያኖች ላይ የፈለገውን ሁሉ ለማድረግ ቢችል ኖሮ እስከዛሬ ድረስ ፈጽሞ ባጠፋን ነበር:: ጌታ በምህረቱ እየጠበቀና በደሙ እየሸፈነ፣ እኛ ካላየናቸው ፍላጻዎቹ እንኳ ጠብቆ እዚህ አድርሶናል:: ነገር ግን አልጠፋንም ማለት መድረስ የሚገባን ደረጃ ደርሰናል ማለት አይደለም:: ልናስተውል የሚገባን ነገር ሰይጣን መክሊታችን የሚቀብርበትን መንገድ ከመፈለግ እንደማይተኛ ነው:: ስለዚህም በአሰራሩ እንዳንታለልና ወጥመዱ ውስጥ እንዳንገባ ከመቸውም የበለጠ ልናስተውል ይገባናል::

ማንኛውም የጠላት አሰራር መግቢያ በር አለው:: ያንንም በር የምንከፍትለት እኛው ነን:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ተፈጸመ» በማለት ድሉን ባወጀልን ጊዜ የሰይጣንም ነገር እንዳከተመለት እሙን ነው:: ነገር ግን ያንን ስልጣናችንን ይዘን በእውነት ካልተመላለስን በርን ያገኛል:: የሚመጣውም ሊያርድና ሊያጠፋ ነው (ዮሐ. 10:10):: ምናልባት አሁን ካለንበት የጸጋ አገልግሎት በበለጠ ሁኔታ ጌታን እንድናገለግለው ይሆን የተጠራነው? ምናልባትስ ለጠላት አሰራር ክፍት ሆነን በመገኘታችን መክሊታችን ተቀብሮ ይሆን? ጸጋችን በሙላት እየተገለጠ ለመሆኑ እርግጠኞች ነን? ግሩም ጥያቄዎች ናቸው:: እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ካስፈለገን፣ ሰይጣን ወደ አገልጋዮች ቀርቦ ጸጋቸውን ለማስጣል ሲነሳ ከምናያቸው ምልክቶች ዋና ዋናዎቹንና የተለመዱትን መመልከቱ መልካም ነው:: የጠላት አሠራር በሕይወቴ እንዳለ በምን አውቃለሁ? ለሚል አገልጋይ የሚከተሉትን ነጥቦች ሰንዝሬ አልፋለሁ::

### *1. ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ቅንአት*

*«የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ፣ ክፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አሰቃየው» (1ሳሙ. 16:14)::*

ሳኦል እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ በበደለ ጊዜ መንግስቱ ከእርሱ ተቀምቶ ለዳዊት ተሰጠ:: ከዚያም የምንመለከተው ክፉ መንፈስ ወደ እርሱ ቀርቦ ሲያሰቃየው ነው:: ይህ የሰይጣን አሰራር በርን አግኝቶ ወደ ሳኦል ሕይወት በቀረበ ጊዜ በሳኦል ላይ ከታዩት ለውጦች አንዱና የከረረው፣ ቅንዓት ነበር:: በዳዊት ላይ ይመቀኝና ይቀናበት ጀመር::

ቅንዓትንና የርኩሳን መናፍስትን አሰራር ግኑኝነት በዚህ ክፍል እንማራለን:: አንድ የእግዚአብሔር ሰው በሕይወቱ ካለማቋረጥ በቅንዓት መንፈስ የሚቃጠል ከሆነ ራሱን ሊመለከትና ለጠላት የከፈተውን በር ለመዝጋት ፈጣን እርምጃ ሊወስድ ይገባዋል:: ይህ ብዙዎቻችን ከጠላት አሰራር ጋር አያይዘን ያልተመለከትነው ጉዳይ ነው:: ስለዚህም በቤተክርስቲያን ውስጥ አሳሳቢ ችግር ሆኗል:: አገልጋዮችን እየጠላንና እየተመቀኘናቸው እንዴት በረከትን እንጠብቃለን?



በቅንዓትና በምቀኝነት ተሞልተን ጌታ በየት አልፎ ጸጋችንን ሊያወጣው ይችላል? እንግዲህ እናስተውል:: ቅንዓትና ምቀኝነት አደገኛ ጠላት የሚጠቀምባቸውና መክሊታችንን የሚያስቀብሩ አጋንንታዊ አሰራሮች ናቸውና በጌታ ስም እንቃወማቸው::

በአገልግሎት አከባቢ ላሉ ወገኖች ሁሉ የሚከተሉትን ሦስት ሁኔታዎች አስመልክቶ ከቅንዓት መንፈስ ራሳቸውን እንዲያጠሩ እመክራለሁ::

*ሀ) በአቻዎቻችን ላይ አንቅና::* አቻዎቹ የቀኑበት ሰው ምሳሌ ዮሴፍ ነው:: አብሮ አደግ ወንድሞቹ ቀንተው ያደረጉበትን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ መዝግቦልናል:: *«የአባቶችም አለቆች በዮሴፍ ቀንተው ወደ ግብፅ ሸጡት» (ሐዋ. 7:9)::* ዮሴፍን የቀኑበት አቻዎቹ የሆኑ ወንድሞቹ ናቸው:: እንደእውነቱ ከሆነ ዮሴፍ ብቻ አልነበረም ለአለቅነት የተጠራው:: ወንድሞቹም ለአለቅነት ተጠርተው ነበር፤ ቃሉ «የአባቶችም አለቆች» ብሎ ጠርቷቸዋልና:: የጥሪያቸው አቅጣጫና የአለቅነታቸው በትር ግን የተለያየ ነበር:: ዮሴፍን የጠራ አምላክ እነርሱን ጠርቷቸው ነበር:: ጥሪያቸው የሚገለጥበት ጊዜና የሚወስዳቸው ጎዳና ግን የተለያየ ነበር:: ይህን ምስጢር ስላላስተዋሉ ነበር የቀኑበት::

ጌታ ባጠገባችን ያስቀመጠውን አገልጋይ ሲሾመውና ሲቀባው ስንመለከት አንቅና:: ለእኛም ጌታ አላማ አለውና ያንን ከመፈጸም የሚከለክለው የለም:: ምናልባት ወንድሞቹ ዮሴፍን እንደታናሽ ሳይቆጥሩት እንዳልቀሩ፣ ጌታ እያስነሳው ያለው ሰው በብዙ ነገር ከእኛ በታች ነው ብለን እናስብ ይሆናል:: ማስተዋል ያለብን ነገር ግን የሚያሳድግ እግዚአብሔር መሆኑን ነው:: ልባችንን ጠብቀን ጌታ ለእኛ ያዘጋጀውን ጊዜና መንገድ ብንጠብቅ በድንቅ ያወጣናል::

*ለ) በብላቴኖች ላይ አንቅና::* ከዚህ ክፍል መግቢያ ላይ እንደተመለከትነው ሳኦል በትንሹ በዳዊት ላይ እንደቀና ተገልጧል:: *«ከዚያንም ቀን ጀምሮ ሳኦል ዳዊትን ተመቅኝቶ ተመለከተው» (1ሳሙ. 18:9)::* ሳኦል ዳዊትን ከልጅነቱ ጀምሮ ሳያውቀው አይቀርም:: እርሱ ሲቀባና በተለያዩ የውጊያ ዘመናት ሲያልፍ ዳዊት ገና ብላቴና እረኛ ነበር:: ነገር ግን ዳዊትም እንደአቅሙ የራሱ የሆነ ልምምድ የነበረው ሰው ነበር:: ጊዜው ደርሶ ጌታ ሲያወጣው ሳኦል ደስ አልተሰኘም:: እርሱ በብዙ ልምምድ ያሳለፈው ሰው እያለ ጌታ እንዴት በብላቴናው ሊጠቀም ይችላል?

ትናንት በብላቴንነታቸው የምናውቃቸውን ክርስቲያኖች ዛሬ ጌታ ሲቀርባቸውና ሲያስነሳቸው ስናይ የቅንዓት መንፈስ እንዳይቀርበን አጥብቀን ልባችንን እንጠብቅ:: ጌታ ለእኛ የሰጠንን ጸጋችንን ለመጠበቅ ያልተጋን ሰዎች፣ ጸጋቸውን አክብረው በመክሊታቸው ለማትረፍ በሚነሱት ላይ በምቀኝነት እንዳንተጋ እንጠብቅ:: እንግዲህ የጠላትን አሠራር እንወቅበት:: ጸጋችንን ሊያስጥለን ከሚችለው ቅንዓት ከተሰኘው የጠላት ተንኮል ንስሀ እንግባ::

*ሐ) በበላዮቻችን ላይ አንቅና::* ሙሴ የተሰኘው ታላቅ የሕግ ሰው ከበታቹ በነበሩ ሰዎች በቅንዓት የተገፋ ሰው ነበር:: *«በውን እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሯልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን» (ዘኍ. 12:2)?* እነዚህ ቃላቶች የወጡት የሙሴ ረዳት ከነበሩት ከማሪያምና ከአሮን አንደበት ነበር:: ሙሴ በእነርሱ ላይ ተሹሞ የነበረ አገልጋይ ሆኖ ሳለ ያንን ሁኔታ ያቃለሉና በእርሱ ላይ የቀኑ ሰዎች ነበሩ:: ሁኔታውም እግዚአብሔርን አስቆጣው::

በተለያዩ ጊዜአትና ስፍራዎች ስናገለግል ጌታ በበላያችን የሚያስቀምጣቸው ሰዎች እንዳሉ ማስታወስ አለብን:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ለእነዚያ ሰዎች ጌታ የሰጣቸውን ክብር፣ ሰዎች ለእነርሱ ያላቸውን መልካም አመለካከት፣ አቀባበልና ውጤታማነታቸውን አይተን ልንቀናና ልንመቀኝባቸው አይገባንም:: እነርሱን በታማኝነታቸው ያከበራቸው ጌታ እኛም በታማኝነት ብንጸና ያከብረናል:: ልባችንን ግን ከዚህ ቅንዓት ከሚሉት ሠይጣናዊ አሰራር ልንጠብቅ ይገባናል::

## *2. ጥድፊያ የታከለበት ውሳኔ*

*«ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሳ፣ እስራኤልንም ይቆጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው» (1ዜና. 21:1)::*

እግዚአብሔር ጨዋ አምላክ ነው:: በአደራረጉም እጅግ የሚመች፣ የተረጋጋና ጤናማ የሆነን ሥራ የሚሰራ አምላክ ነው:: የዕቅድ አምላክ ስለሆነም ሰዎችን አያጣድፍም:: ሁሉን በጊዜውና በአላማው ይፈጽማል:: እንግዲህ ይህ የዓላማ አምላክ ዳዊትን ከጠላቶች ሁሉ ላይ ድልን እየሰጠው በሰላም ሲባርከው ሳለ ነበር አንድ ድገተኛ ሃሳብ ወደ ዳዊት አእምሮ መጥቶ ወደ ውሳኔ ያጣደፈው:: የዳዊት ኃጢአት ሕዝቡን መቁጠሩ አልነበረም:: ያ ቢሆን ኖሮ ሙሴ ኃጢአትን አድርጎ ነበር፣ በዘኁልቁ ውስጥ እንደምናነበው የበረሃ ጉዞአቸውን ሲጀምሩና ሲያጠናቅቁ ሕዝቡ እንደተቆጠሩ እናውቃለን:: ዳዊትን ሰይጣን ያነሳሳው በጌታ ከመታመን ይልቅ በብርታቱና ባለው የሰው ኃይል እንዲመካ ነበር:: ኃጢያቱ እዚያ ላይ ነው::

አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮች ሲዋከቡ ይታያሉ:: ከውሳኔ ወደ ውሳኔ፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ፣ ከቤተክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሁም ከጓደኝነት ወደ ጓደኝነት በብርሃን ፍጥነት ሲሯሯጡ ይታያሉ:: ጌታ ባስቀመጣቸው ስፍራ በእምነት ሁኔታዎችን ለመለወጥ ከመነሳት ይልቅ፣ መፍትሄ ይሆኑልኛል የሚሏቸውን ሁኔታዎች ለማድረግ ይዋከባሉ:: የጠላትን አሠራር ከምንለይበት መንገድ አንዱ የምንወስናቸው ውሳኔዎች የተቻኮሉ በመሆናቸውና ባለመሆናቸው ነው:: ጥድፊያ፣ ውክቢያና ግራ መጋባት ከእግዚአብሔር አይደሉም:: ይህን ያስተዋለ አገልጋይ ራሱን በማረጋጋት፣ «ሰይጣን ሆይ ስማ! እንበረከካለሁ፣ ምንም እርምጃ ከመውሰዴ በፊት ጌታ የሚለኝን አዳምጣለሁ» በማለት በረጋ መንፈስ ጠላቱን ያሳፍራል::

ከዚህ በመቀጠል ጠላት አገልጋዮችን ወደ ተጣደፈ ውሳኔ ለማስገባት የሚጠቀምባቸው ሁኔታዎች እንመልከት::

*ሀ) በሰዎች ግፊት የሚመጣ ውክቢያ::* ሰው ሰውን የማሳመን ችሎታ አለው፤ ወይ ለመልካም፣ ወይም ደግሞ ለክፉ:: አንዳንዶቻችን ከሌሎች በምንሰማው ነገር ቁጥር ልክ ሃሳባችንን እንቀያይራለን:: ስለዚህም ጠላት ሰዎችን ተጠቅሞ እኛን ወደተጣደፈ ውሳኔ ማስገባት እጅግ ይቀልለዋል:: እናስተውል፣ እግዚአብሔር የመንግስቱን ተግባር ለማከናወን ሰዎችን እንደሚጠቀም ሁሉ (ዓለማውያንን ጭምር)፣ ሰይጣንም አገልጋዮችን ለማሰናከል ተግባሩን ለመፈፀም የሚጠቀመው ሰዎችን ነው (ክርስቲያኖችንም ጭምር):: *«ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ» (ኤፌ. 5:6)::* *«ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ . . . በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ» (ቆላ. 2:4-8)::*



*ለ) ከሕልም ብዛት የሚመጣ ውክቢያ::* ውጥናችን በበዛ መጠን ለከንቱ ሕልም እንደምንጋለጥ ሲያስተምረን ቃሉ እንዲህ ይላል:- *«ሕልም በስራ ብዛት ይታያል» (መክ. 5:3)::* ነቢዩ ኤርሚያስም እውነተኛ ሕልም የመኖሩን ያህል ውሸተኛም ሕልም እንዳለ ሲያስታውሰን:- *«እናንተም የምታልሙትን ሕልም አትስሙ» ይለናል (ኤር. 29:8)::* ሃሰተኛ ሕልም ጠላት ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው:: ስለዚህም መጀመሪያውና መጨረሻው ያልተያዘና ያልተጨበጠ ሕልም ባየን ቁጥር ለውሳኔ የምንሮጥ ሰዎች ጠላት ኢላማ ውስጥ ራሳችንን እያስገባን ነውና እናስተውል::

*ሐ) ከሁኔታዎች መለዋወጥ የሚመጣ ውክቢያ::* ጠላት አገልጋዮችን ከጌታ ፈቃድ ለማስወጣት ከሚያንቀሳቅስበት መንገድ አንዱ ሁኔታዎችን በመጠቀም ነው:: አንዳንድ ጊዜ በጌታ ፈቃድ ውስጥ እያለን ሁኔታዎችን ዝግትግት ያደርግብናል:: ሰው ሁሉ በጠማማ እንዲመልስልን ይገፋፋል:: ጉዳዮቻችን የማይፈጸሙ፣ ወዳጆቻችን ለእኛ ግድ የሌላቸው፣ አገልግሎት ሁሉ እንደጌታ ፈቃድ ያልሄደ አድርጎ ሊያሳየን ይሞክራል:: እንግዲህ ቁም ነገሩ እዚህ ላይ ነው:: በእነዚህ ሁኔታዎች ተገፋፍቶ ወደ ውሳኔ የሚጣደፍ ሰው ራሱን ለጠላት ተንኮል ያጋልጣል:: ነገር ግን፣ ባለሁበት ስፍራ ያስቀመጠኝ ጌታ ነው ስለዚህም በማየው ነገር ሳልወሰድ እርሱ እስኪያነሳኝ ድረስ እጠብቀዋለሁ በማለት በተረጋጋ መንፈስ በጌታ ፊት የሚወድቅ ሰው በድል ይወጣል:: *«እንግዲህ ሁልጊዜ ታምነን፣ በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና» (2ቆሮ. 5:7)::*

## *3. ክስና ፍርድ*

*«እርሱም ታላቁን ካህን ኢያሱን በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ አሳየኝ፣ ሰይጣንም ይከስሰው ዘንድ በስተ ቀኙ ቆሞ ነበር» (ዘካ. 3:1)::*

ታላቁ ካህን ኢያሱ እድፍ የሞላበት ልብስ ተከናንቦ እንደነበር እሙን ነው:: ይህንንም ሁኔታ በማስታከክ ነበር ጠላት ሊከስሰው የተነሳው:: ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሔር ግን ኢያሱን አልተወውም ነበር:: ጠላትን ገሰፀው:: ኢያሱም በእግዚአብሔር ፀጋ የቆመ አገልጋይ መሆኑን መሰከረለት:: አበሳውን አርቆና ቆሻሻውን ልብስ አስወግዶ ጥሩ ልብስ አጎናጸፈው::

ክስ ከሠይጣን መሳሪያዎች አንዱና ዋነኛው ነው:: የኃጢያት ሁሉ ምንጭ ሰይጣን ነው:: ሰይጣን ሰዎችን ያስታቸዋል:: ካሳታቸው በኋላ ደግሞ ስለሰሩት ኃጢያት ካለማቋረጥ ይከሳቸዋል:: ስለዚህም በሕይወቱ ክስ የሞላበት ማንኛውም አገልጋይ የጠላት አሠራር ወደ ሕይወቱ እየቀበረ እንደሆነ ሊያስተውል ይገባዋል:: አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን ካለማቋረጥ ስንከስ እንገኛለን:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ሰዎችን በክስ እናደክማቸዋለን:: በዚህም ተግባራችን ራሳችንን ለጠላት አሰራር አጋልጠን እንሰጣለን::

*«ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሏልና» (ራዕ. 12:10)* እኛም የክስን ሕይወት ልንጥል ተጠርተናል:: ይህንንም ለማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ የክስ ሕይወት ወደ አገልጋዮች ለማምጣት ጠላት የሚጠቀምባቸውን መንገዶች ማወቁ ጠቃሚ ነው:: የሚከተሉት ሁኔታዎች ለጠላት ክስ በርን ይከፍታሉ::

ይህ የመጽሐፋችን መደምደሚያ ምእራፍ ነው። ይህ ምእራፍ አንድን ታላቅ እውነት ያስታውሰናል። ይህም እውነት ጸንቶ መቆም ነው። ከሚከተሉት ሕይወታችንን ሊያናጉና መከሊታችንን ሊቀብሩ ከሚነሱ ጠንቆች ልንጠበቅና ጸንተን ልንቆም ይጠበቅብናል።

1. የስደት እሳት።
   የስደት እሳት ከሚከተሉት አቅጣጫዎች ይነሳል።
   ሀ) ለጌታ የቀኑ ከሚመስላቸው የሚመጣ ስደት።
   ለ) ከመስቀሉ ጠላቶች የሚመጣ ስደት።
   ሐ) ከስሜት መዛባት የሚመጣ ስደት።

2. ዓለምን ማፍቀር።
   ዓለምን ማፍቀር በሶስት መልኩ ሊገለጥ ይችላል፡-
   ሀ) የዓለም ጥበብ።
   ለ) የዓለም ርኩሰት።
   ሐ) የዓለም ትምህርት።

3. ሃሰተኛ ነቢያት።
   ሃሰተኛ ነቢያት የሚከተሉት ገጽታዎች አሏቸው፡-
   ሀ) ያልተገራው ነቢይ።
   ለ) ያበደው ነቢይ።
   ሐ) ያልተቀባው «ነቢይ»።

4. ያለመታዘዝ ችግር።
   አለመታዘዝን ከሚያስከትሉ መዘዞች የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡-
   ሀ) ውጤት አልባነት።
   ለ) መሰናከል።
   ሐ) ዝቅተኝነት።

5. ጉስቁልና።
   የሚከተሉት ነጥቦች የመከራን አይነቶች ያሳዩናል፡-
   ሀ) ከግፍ የሚመጣ መከራ።
   ለ) ከኃጢአት የሚመጣ መከራ።
   ሐ) ከመልካምነት የሚመጣ መከራ።

*ሐ) ከስሜት መዛባት የሚመጣ ስደት::* ይህ ዓይነቱ አገልጋይ ማንም ሳያሳድደው ሁሉም ሰው በእርሱ ላይ የተነሳ የሚመስለው ሰው ነው:: ስሜቱ ስለተዛባ አስተሳሰቡም ተናግቷል:: ሁለት ሰዎች ወደ እርሱ እየተመለከቱ ሲያወሩ ስለ እርሱ ክፉ ነገር የሚያወሩ ይመስለዋል:: ዘወትር እርሱ በሌለበት ስለእርሱ የሚወራና ሰው ሁሉ ያደመበት ይመስለዋል:: ይህ ሰው በጌታ አይታመንም፣ ራሱን አይተማመንም፣ ሌሎችንም አያምንም፤ ዘወትር የስጋት ህይወት የሚያሳልፍ ሰው ነው:: ይህ ሁኔታ የጠለቀ ችግር ምልክት ነውና ሊታሰብበት ይገባል:: ቃሉ፣ *«ኃጥእ ማንም ሳያሳድደው ይሸሻል» (ምሳ. 28:1) ይላልና፣* ይህ ችግር ያለበት አገልጋይ በቅድሚያ የግሉን ህይወት በመመልከት ሁልጊዜ እንዲሰጋ ያደረገው ኃጢያት ካለ ንስሃ ሊገባ ያስፈለገዋል:: እግዚአብሄር እርሱን ስለሚዘነጉ ባሪያዎቹ፣ *«በነፋስም የምትንቀሳቀስ የቅጠል ድምጽ ታሸብራቸዋለች» (ዘሌ. 26:36)* ሲል ባህሪያቸውን ይገልጻል:: ይህ እንዳይሆን በቅድሚያ ራስን መመርመርና ማንኛ ውንም ኃጢያት ማስወገድ ይኖርብናል:: ከዚያም በመቀጠል፣ ሰዎች ሊቀበሉንም ላይቀበሉንም እንደሚችሉ መገንዘብ አስፈላጊ እርምጃ ነው:: ሰዎች ከተቀበሉን መልካም፣ ካለዚያም ኢየሱስ ተቀብሎናል ታምነን እንስማራ::

*«በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በስጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በስጋችን ተሸክመን እንዞራለን» (2ቆሮ. 4:8-10)::*

## *2. ዓለምን ማፍቀር*

*«በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ፤ ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና» (2ጢሞ. 4:9-10)::*

ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዴማስን ስም የምንመለከተው በቆላስያስ 4:14 ነው:: ከዚያም በፊሊሞና 1:24 ላይ ጳውሎስ አብረው የሚሰሩትን አገልጋዮች ሲጠቅስ ከማርቆስ፣ ከአርስጥሮኮስና ከሉቃስ ጋር የዴማስ ስም ተጠቅሷል:: ማርቆስና ሉቃስ በተሰጣቸው ፀጋ ለጌታ ክብር ለመቆማቸው ማብራሪያ አያስፈልገውም:: አርስጥሮኮስም ቢሆን እስከ እስር ቤት ድረስ ከጳውሎስ ጋር ቆሞ የፀና የክርስቶስ ባሪያ ነው:: እንግዲህ ከእነዚህ መካከል ሲያገለግል የነበረው ዴማስ ነው «የአሁኑ ዓለም» ወዶ ጸጋውን የጣለው::

ዓለማዊነት አደገኛ ጠንቅ ነው:: ጸጋን ያስጥላል:: መክሊትን ያስቀብራል:: ዓለማዊነትን በአንድ እጃቸው ይዘው በሌላኛው እጃቸው ጌታን አከብረዋለሁ የሚሉ ሰዎች በእድሜያቸው ይቀልዳሉ:: ዓለማዊነት መልኩን በተለያየ ሁኔታ ይገልጻል:: ጸጋችን በሙላት እንዳይወጣ ምን ዓይነት ሁኔታ እያታለለን ነው? ምን የተያዝንበት ነገር አለ? እናስተውል! ከክርስቶስ ወንጌል ጋር የማይሄድ አንዳች ነገር በህይወታችን ካለ ዛሬውኑ በጣጥሰን እንጣለው:: አለበለዚያ ለጌታ ክብር በሙላት ልንቆም አይቻለንም:: ራሱን ለጌታው የሰጠ አገልጋይ በውስጡ የሞላው የጌታ ቅባት በሙላት እንዲወጣ ከፈለገ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አስመልክቶ ከዓለማዊ መርዝ ራሱን ሊጠብቅ ይትጋ::

*ሀ) የዓለም ጥበብ::* *«ጥበበኛ የት አለ? ፃፊስ የት አለ? የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ምኝነት እንዲሆን*



*አላደረገምን? በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበቧ ስላላወቀች፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗልና» (1ቆሮ. 1:20-21)::*

*አገልጋይ የስብከትን ሞኝነት ተወት በማድረግ ወደተለያዩ ሰው ሰራሽና ዓለማዊ ጥበቦች ዘወር ሲል ጸጋውን ይጥላል:: በዓለማዊ ብልሃትና ጥበብ ጌታን ልናየው አንችልም:: አንድን ነገር አንዘንጋ፣ ወንጌል አንድና ቀላል ነው:: እግዚአብሔር ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ልጁን ኢየሱስን ላከው:: ልጁ ኢየሱስም በእርሱ የሚያምን ሁሉ ደህንነትን ያገኝ ዘንድ ሞተ ተቀበረ፣ ከሙታንም ተነሳ:: ዳግም ለፍርድ እስኪመለስም ድረስ በአብ ቀኝ ሆኖ ስለ እኛ ይማልዳል:: እኛም የዚህ ወንጌል ምስክሮች ልንሆን ተጠርተናል:: እንግዲህ ይህን ወንጌል ነው ሰው በተለያዩ የጥበብ መጋዝ ሲሰነጠቅ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ መውጣት ያልቻለችበት መዘዝ ውስጥ የገባችው:: አገልጋይ ሆይ፣ ጸጋህ በሙላት እንዲወጣ ትፈልጋለህ? ይህ ዘመን ባመጣብን ዓለማዊ ጥበብ እንዳትበከል ልብህን ጠብቅ:: «ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ ምንም በዚች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን:: የዚች ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና:: እርሱ ጥበበኞችን በተንኰላቸው የሚይዝ፤ ደግሞም፣ ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ከንቱ እንደ ሆነ ያውቃል ተብሎ ተጽፏልና» (1ቆሮ. 3:18-20)::*

*ለ) የዓለም ርኩሰት::* ይህች ዓለም በክፉ ተይዛለች:: በተለይም ባለንበት ዘመን ሰውን ሳያስበው ወደርኩሰት ውስጥ የሚከቱ ብዙ ቆሻሻ ነገሮች ተፈጥረዋል:: እንግዲህ አገልጋይ ካለማቋረጥ ራሱን ከዚህ ቆሻሻ ካልጠበቀ ጸጋው ይዳፈናል:: የተሰጠውን መክሊት በሙላት ለመጠቀምና ለማትረፍ የሚተጋ አገልጋይ ከዓለም ርኩሰት የተለየ አገልጋይ ነው:: የዚህም ውሳኔ የመጀመሪያው እርምጃ በቤተ ክርስቲያን ካሉ ርኩሰትን ከሚለማመዱ ሰዎች መራቅ ነው::

*«ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ:: በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞችን፣ ወይም ገንዘብን የሚመኙትን ነጣቂዎችንም፣ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩትን አላልሁም፤ ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር:: አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ፣ እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ» (1ቆሮ. 5:9-11)::*

*ሐ) የዓለም ትምህርት::* በዓለም ውስጥ ሳለን ለተለያዩ የክርስቶስን እውነት ለሚቃወሙ ትምህርቶች ልንጋለጥ እንችላለን:: አንዳንድ ጊዜም የጌታ ቃል እንዲለውጠን ራሳችንን ከምንከፍትበት በበለጠ ሁኔታ ለእነዚህ ዓለማዊ ትምህርቶች ራሳችንን ከፍተን እንገኛለን:: በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ የዓለም ትምህርት አይሎ የክርስቶስ ወንጌል እውነት ኃይሉን በሙላት በእኛ መግለጥ የሚሳነው:: እውነተኛ አገልጋይ አይኑን በመስቀሉ ላይ የተከለ፣ አእምሮውን በቃሉ ያደሰና ልቡን በጌታ እምነት ላይ ያሳረፈ ሰው ነው:: *«እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፣ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ» (ቆላ. 2:8)::*

## *3. ሃሰተኛ ነቢያት*

*«እርሱም፣ ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ና፣ እንጀራም ብላ አለው:: እርሱም ከአንተ ጋር እመለስና እገባ ዘንድ አይቻለኝም በዚህም ስፍራ ከአንተ ጋር እንጀራ አልበላም፣ ውኃም አልጠጣም በዚያ እንጀራ አትብላ ውሃም አትጠጣ፣ በመጣህበትም መንገድ አትመለስ በሚል በእግዚአብሔር ቃል ተቀብሎልኛልና አለ:: እርሱም፣ እኔ ደግሞ እንደ አንተ ነቢይ ነኝ መልአክም፣ እንጀራ ይበላ ዘንድ ውኃም ይጠጣ ዘንድ ከአንተ ጋር ወደ ቤትህ መልሰው ብሎ በእግዚአብሔር ቃል ተናገረኝ አለው:: ዋሸቶም ተናገረው ከእርሱም ጋር ተመለሰ፣ በቤቱም እንጀራ በላ ውሃም ጠጣ» (1ነገ. 13: 15-19)::*

በዚህ ታሪክ ውስጥ የሁለት ነቢያት ድራማ ይታያል:: ከይሁዳ ወደ ቤቴል የተላከው ነቢይ «የእግዚአብሔር ሰው» ተብሎ ተጠቅሷል:: በቤቴል የነበረው ነቢይ ደግሞ፣ «ሽማግሌ ነቢይ» በመባል ይታወቃል:: ከታሪኩ እንደምንረዳው ከይሁዳ ወደ ቤቴል ተልኮ የነበረው ይህ ነቢይ በመንገድ ላይ የውኃንም ሆነ የምግብን ግብዣ እንዳይቀበል፣ በመጣበትም መንገድ እንዳይመለስ በእግዚአብሔር ታዞ ነበር:: በቤቴል የነበረው ሽማግሌ ነቢይ ግን የሃሰትን ትንቢት በመናገር ቀድሞ ከተነገረው ትዕዛዝ ሲያሳስተው እናነባለን:: ከዚያ በኋላ የነበረው የዚያ «የእግዚአብሔር ሰው» ታሪክ አሳዛኝ ነው:: በመንገድ አንበሳ እንደገደለው እንረዳለን::

ይህን የእግዚአብሔር ሰው በአጭሩ የቀጨው ምንድን ነው? በመርዘኛ ነቱና የአገልጋዮችን ጸጋ በመግፈፉ የታወቀው የሃሰተኛ ነቢያት አሰራር ነው:: ይህ ሁኔታ በዘመናችንም የብዙዎቹን ጸጋ አስጥሏል:: አንዳንዶች የተሳሳተ ውሳኔ ውስጥ ገብተዋል:: ሌሎች ደግሞ የሃሰት ትንቢት በሚናገሩላቸው ሰዎች ታስረው ተቀምጠዋል:: ብዙ የሚያቆስል የሃሰት ትንቢት ከመስማታቸው የተነሳም ከእንግዲህ ወዲያ በቃኝ ብለው ከአገልግሎታቸው የተሰናበቱም አሉ:: ይህን ሁሉ የሚያመጣው የሃሰተኛ የነቢያት መንፈስ ነው:: የሃሰተኛ ነቢያት መንፈስ ጸጋን ያስጥላል፣ መክሊትን ያስቀብራል፣ የሰው ባሪያ ያደርጋል፣ ግራ ያጋባል:: ለመሆኑ የሃሰተኛ ነቢያት መንፈስ ሕይወታቸውን ለከፈቱለት ሰዎች የማያመጣው ምን ችግር አለ?

ጸጋችን በዚህ ክፉ አሠራር ተመትቶ እንዳይወድቅ ሁላችንም ከሚከተሉት ሶስት ዓይነት ሃሰተኛ ነብያት ልንጠነቀቅ ይገባናል:: ከእነርሱ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ ራሳችንም የሃሰተኛ ነቢያት መንፈስ መልእክተኞች እንዳንሆን ልናስተውል ይገባል::

*ሀ) ያልተገራው ነቢይ::* ያልተገራው ነቢይ ከጌታ የተላከና የተቀባ አገልጋይ ሆኖ ሳለ፣ ባህሪው ካለመለወጡና ስለተጠራበት ጥሪና ስለቅባቱ በቂን እውቀት ያላዳበረ በመሆኑ የሚያበላሽ ነቢይ ነው:: ይህ በስጦታ ካለመብሰል፣ ከአዲስነትና እንደሚገባ ካለመማር የሚመጣ ችግር ነው:: ሆኖም ሁኔታው የጠላት መጠቀሚያ ሆኖ በሰዎች ላይ ጉዳት ማስከተሉ አይቀርምና ቃሉ የሚያስተምረንን እናስተውል:: *«የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ፤ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና» (1ቆሮ. 14: 32-33)::*



አንድ አገልጋይ በእግዚአብሔር መንፈስ ለነቢይነት ተቀብቶ ሳለ ካለመብሰልም ሆነ ራስን ካለመግዛት እንዳሻው ሲራመድ ሲገኝ ከዚህ ክፍል ውስጥ ይመደባል:: በእግዚአብር ቃል ያልተገራ ነቢይ በጊዜው ካልታረመ ወደስህተት ማምራቱ አይቀርም:: እውነተኛ ድምጽን ከጌታ ለማፍሰስ የተጠሩ ሆነው ሳሉ ስርዓት ከማጣታቸው የተነሳ ያበላሹ ጥቂቶች አይደሉም:: ያልተገራ ነቢይ ዋነኛ ምልክቱ ሰላምን የሚያናጋ ባህሪይ ማንፀባረቁ ነው:: ቅባቱ፣ መልዕክቱም ሆነ ተልዕኮው ከጌታ ሆኖ ሳለ ያልጎለመሰ ባህሪይ ስላለው ሰላምን ያውካል:: እናስተውል! የእግዚአብሔር አሠራር ሰላም የሰፈነበትና ሰማያዊውን ፍጹምነት የሚያንፀባርቅ ሊሆን ይገባዋልና መንፈሳችንን እንጠብቅ::

*ለ) ያበደው ነቢይ::* ያበደው ነቢይ እግዚአብሔር በተናገረው ላይ የሚጨምር ወይም ከተናገረው የሚቀንስ ነው:: ከዚያም አልፎ ፈጽሞ ያልተሰጠውን መልዕክት ሲናገር ይሰማል:: ይህ ሰው በእግዚአብሔር ለመቀባቱ ጥያቄ የለውም:: ነገር ግን እንደተገለጠው ከእግዚአብሔር ሃሳብ የመውጣት ዝንባሌ አለው:: ይህ ችግር ብዙ ጊዜ በአገልግሎት ከመቆየት የተነሳና «ጌታን ከመልመድ» የሚመጣ ሁኔታ ነው:: ጌታ የሚለመድ አምላክ ላለመሆኑ ነቢዩ በለዓም የዚህ ምሳሌያችን ነው:: *«ቅንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ፤ የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፤ እርሱ የአመፃን ደመወዝ ወደደ፣ ነገር ግን ስለመተላለፉ ተዘለፈ፤ ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ» (2ጴጥ. 2:15-16)::*

አብዛኛውን ጊዜ አንድ ነቢይ ያልተሰጠውን በእግዚአብሔር ስም እንዲናገር የሚገፋው ጥቅም መኖሩ ግልጥ ነው:: ይህንንም ጉዳይ ቃሉ «የአመፃ ደመወዝ» ይለዋል:: ለጥቅማቸው ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል ከሚያጣምሙ ሰዎች መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው:: ከእግዚአብሔር አንደበት ባልወጣ ትንቢትንና መገለጥ ተውጠው ጸጋቸውን የጣሉ ብዙዎች እንዳሉ የሚዘነጋ አይደለም::

*ሐ) ያልተቀባው «ነቢይ»::* እንደተመለከትነው ሁሉ፣ ያልተገራው ነቢይ እውነተኛ ቅባት ኖሮት ሳለ ያልተማረ በመሆኑ ያጠፋል:: እንዲሁም ያበደው ነቢይ የተቀባ ሆኖ ሳለ ነገሮችን መልመዱ ያሳስተዋል:: አሁን የምንመለከተው ግን ከእነዚህ ለየት ያለውን ያልተቀባውን «ነቢይ» ሁኔታ ነው:: ያልተቀባው ነቢይ እንደስያሜው ሁሉ ያልተቀባና ቀድሞውኑም ጥሪውም ሆነ ጸጋው ያልተሰጠው ሰው ነው:: ይህ ሰው ካለጥሪው ገብቶ የሚዘባርቅና የብዙዎችን ሕይወት የሚያበላሽ ሰው ነው:: ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለዚህ ሁኔታ ጠቃቅሶ አልፏል:: *«ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስለው ይህች የፃፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ» (1ቆሮ. 14:37)::*

ይህ ስህተት፣ የነቢይነትን ቅባት ከመመኘትና በስሜት ከመሄድ፣ ያልሆኑትን እንደሆኑ ለመታየት ከመፈለግ፣ የተመኙትን ጥቅም ለማግኘት የጌታን ስም ከመጠቀም ወይም ደግሞ ምስጢራዊ ከሆነ የአጋንንት እስራት ሊመጣ ይችላል:: እናስተውል! መናፍስትንም እንመርምር:: አለዚያ እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠውን ጸጋ እንጥላለን::

## 4. ያለመታዘዝ ችግር

*«እኔም፣ የእግዚአብሔርን ስም አላነሳም፣ ከእንግዲህ ወዲህም በስሙ አልናገርም ብል፣ በአጥንቶቼ ውስጥ እንደ ገባ እንደሚነድድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ፤ ደከምሁ መሸከምም አልቻልሁም» (ኤር. 20:9)::*

አገልጋይ ሆኖ በውስጡ ትግል የሌለበት ሰው አለ ብዬ አላምንም:: በእውነት ለጌታ የተሰጠ አገልጋይ ግን ትግሉን ሁሉ አሸንፎ ይወጣል:: ነብዩ ኤርምያስ አገልጋዮች ከሚያልፉበት የትግል አይነቶች በአንዱ ውስጥ ያለፈ የእግዚአብሔር ባሪያ ነበር:: በውስጡ የሚቃጠለው የእግዚአብሔር መልዕክትና በውጪ የሚያየው ሁኔታ እየተጋጨበት አስቸገረው:: ስለዚህም በእግዚአብሔር ስም ላለመናገር ሲታገል ይታያል::

እግዚአብሔር ወዳሰማራው የአገልግሎት መስክ ላለመሰማራት እምቢ በማለት የሚታገል አገልጋይ ውጤት አያምርም:: አገልጋዮች በተለያዩ ምክንያቶች ከተሰጣቸው አደራ ይሸሻሉ፣ መክሊታቸውንም ይቀብራሉ:: ብዙውን ጊዜ መክሊታቸውን የሚጥሉ አገልጋዮች የራሳቸው በቂ የሚመስሉ ምክንያቶች አሏቸው:: ጌታ ግን ሲቀባን የሚያረገውን የሚያውቅ አምላክ ስለሆነ ምንም ምክንያት በፊቱ በቂ አይደለም:: ከዚህ በታች የምንመለከታቸው ምክንያቶች በዘመናችን ከሚሰጡት ምክኒያቶች ጥቂቶቹ ናቸው::

*ሀ) ውጤት አልባነት::* አንዳንድ ጊዜ ጮኸን ጮኸን የሚሰማን ያጣን ሲመስለን፣ «በቃኝ፣ እምቢ» ለማለት ይቃጣናል:: ስለዚህም ውስጣችን፣ «ማንም የሚሰማኝ የለም፣ ብቻዬን ነው በከንቱ የምደክመው» እያለ ሲያጉረመርም በእግዚአብሔር ፊት ይሰማል:: ተናግረን ተናግረን ማንም ሲያደምጠው ያልፈለገው ማስጠንቀቂያችን ሲደርስ፣ መልካሙንም ለማድረግ ተግተንና ደክመን ፍሬ ቢስ የሆንን ሲመስለን፣ እንዲሁም ደግሞ እኛ በቁም ነገር የተጋንለትን ነገር ሌሎች በፌዝ እንደያዙት ስናስብ፣ ውስጣችን ይደክማል:: ስለዚህም እኛም እንደ እስራኤል ልጆች፣ *«እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው፤ ትእዛዙንስ በመጠበቅ፣ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ፊት ኀዘንተኞች ሆነን በመሄድ ምን ይረባናል?» (ሚል. 3:14)* ማለት ይቃጣናል::

የእግዚአብሔር የጥሪ እሳት ግን ከውስጣችን እንዳልጠፋ እኛው እናውቀዋለን:: አላስቀም አላስቀምጥ እያለ በውስጣችን የሚነድ የመንፈስ ቅዱስ እሳት አለ:: እንዴት ብለን ይህን የጥሪ እሳት ትተን እንሄዳለን:: እንበርታ፣ እንጠንክርም:: እግዚአብሔር የሚሰራውን የሚያውቅ አምላክ ነውና እንታክት::

*ለ) መሰናከል::* ቤተ ክርስቲያንና አገልግሎት እስካሉ ድረስ ይሄ መሰናከል የሚሉት ችግር ፈጽሞ የማይጠፋ ሁኔታ እንደሆነ ቃሉም ሆነ ልምምድ ይነግረናል:: በተለይም በዚህ በመጨሻው ዘመን ይህ የመሰናከል ችግር ብዙዎችን እንደሚያጠቃ ክርስቶስ:- *«በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ» (ማቴ. 24:10)* ሲል አስቀድሞ ተናግሯል:: ይህ ችግር ሊመጣ የሚገባው የተተነበየለት ጉዳይ ነው:: እውነት ነው፣ *«መሰናከል ግድ ሳይመጣ አይቀርም» (ሉቃ 17:1)::*

ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባን ጥያቄ ይህ ነው:- «ትንቢት የሚፈጸምብኝ አገልጋይ መሆን ነው የምፈልገው፣ ወይስ የሚፈጽምልኝ?» በአንዳንዶች



አገልጋዮች ላይ ይህ ትንቢት እየተፈጸመባቸው ነው:: ከአገልግሎትም እምቢ ብለው ይወጣሉ:: የዚህ የመጨረሻው ዘመን መንፈስ አሠራር አልተገለጠላቸውምና ይሰናከላሉ:: ስለዚህም ወደ ስህተት ያመራሉ:: መቼ ይሆን ይህን መሰናከል የሚሉትን ነቀርሳ ቤተ ክርስቲያን አሸንፋ በዚያ ጠንቅ ምክንያት ከአገልግሎት የሚርቁትን ሁሉ በክንፎቿ ሰብስባ የምናያት?

*ሐ) ዝቅተኝነት::* ራሱን ካለልክ ዝቅ የሚያደርግ አገልጋይ ተቀብቶ ሲላክ አይቼ አላውቅም:: ይህን ሃሳብ አስመልክቶ ሦስት አይነት አልጋዮች አሉ:- 1) ትዕቢተኛ፣ 2) ትሁትና 3) ያለልክ ራሱን የሚያዋርድ:: ትዕቢተኛውን አገልጋይ እግዚአብሔር ይቃወመዋል ጸጋውንም እርሱ ላይ አያባክንም:: ትሁቱን አገልጋይ ግን በጸጋ ላይ ጸጋ ያጎናጽፈዋል:: ካለልክ ራሱን ዝቅ የሚያደርገው አገልጋይ ግን በእውነተኛ ትህትናው ዘመን የተቀበለውን ጸጋ የሚጥል አገልጋይ ነው::

አገልጋይ ሆይ፣ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 4 መሰረት አበረታታለሁ:: ራስህን ካለልክ ዝቅ ከማድረግ የተነሳ *«ማንም ታናሽነትህን አይናቀው» (ቁ. 12)::* ይህ ማለት ደግሞ ካለምንም ዕድገት ባለህበት ሂድ ማለት እንዳልሆነ አትዘንጋ:: እግዚአብሔር በሚሰጥህ ጸጋ *«ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ ይህንንም አዘውትር» (ቁ. 15)::*

## 5. ጉስቁልና

*«ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፣ ኢዮብንም ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቁስል መታው:: ሥጋውንም ይፍቅበት ዘንድ ገል ወሰደ፣ በአመድም ላይ ተቀመጠ:: ሚስቱም፣ እስከ አሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ስደብና ሙት አለችው» (ኢዮ. 2:7-9)::*

ችግርና ጉስቁልና የብዙዎችን አገልጋዮች ጸጋ ያስጣለ ሁኔታ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ችግር መንፈሳዊነት ይመስላቸዋል:: ተሳስተዋል! በችግር ውስጥ እምነትንና ጸጋን ሳይጥሉ ማለፍ ነው መንፈሳዊነት እንጂ ችግረኛ መሆን በራሱ መንፈሳዊነት አይደለም:: ኢዮብ በታላቅ ጉስቁልና ውስጥ ሲያልፍ ጸጋውን የሚያስጥል ድምጽ ወደ እርሱ እያስተጋባ ነበር:: ይህም ድምጽ የመጣው በሚስቱ በኩል ነው::

ሕይወታችን በምን ሁኔታ ነው ያለው:: ጉስቁልና እያንገላታን ነው? «እግዚአብሔር ካከበረኝና ለአገልግሎት ከመረጠኝ ለምን በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳልፍ ፈቀደ?» እያልን ከራሳችንና ከወዳጆቻችን ጋር እንጨዋወታለን? ብቻችንን አይደለንምና አንፍራ:: በዓለም ዙሪያ ያሉ የክርስቶስ ባሪያዎች ሁሉ ያለፉበትንና አሁንም የሚያልፉበትን ጉስቁልና እናስብ:: ቃሉ እንዲህ ሲል እውነትን ይናገረናል:- *«የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፣ እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል» (መዝ. 34:19)::* ይህን እውነት እያሰብን በ1ኛ ጴጥሮስ 2:19-20 መሰረት የምንዘረዝራቸውን የጉስቁልና ምንጮች እናስተውላቸው::

*«በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገስ ምስጋና ይገባዋልና:: ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሱ፣ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሱ፣ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል» (1ጴጥ. 2:19-20)::*

በዚህ ክፍል መሰረት በሦስት አይነት መልኩ አገልጋይ መከራን ሊቀበል ይችላል:: ከሦስቱ የመከራ ምንጮች ሁለቱ አገልጋዩ በትእግስት ካሳለፋቸው ለምስጋና የሚያበቁት ሲሆኑ፣ አንዱ ግን ከጌታ ፈቃድ ውጭ የሆነ የመከራ ምንጭ ነው::

*ሀ) ከግፍ የሚመጣ መከራ::* በግፍ የሚመጣ መከራ ወደ አገልጋይ ከሚመጡት የመከራ አይነቶች አንዱ ነው:: ጴጥሮስ:- *«በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው. . .»* በማለት ሁኔታውን ይገልጠዋል:: አገልጋይ ባላደረገው ነገር ሲከሰስ፣ ሳያጠፋ ስሙ ሲጠፋና ለእግዚአብሔር በየዋህነት ማደሩን ሰዎች ሲጠቀሙበት፣ ያ ሰው በግፍ መከራ ተቀበለ ማለት ነው:: እግዚአብሔር ግን ሁሉን የሚያይና የሚመረምር፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው የሚከፍል አምላክ ነው:: ስለዚህም በግፍ የሚጎሳቆል የእግዚአብሔር ሰው *«እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገስ ምስጋና ይገባዋልና» (ቁ. 19)::*

*ለ) ከኃጢአት የሚመጣ መከራ::* ጴጥሮስ:- *«ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ. . .»* እንዳለው፣ አንድ አገልጋይ ከሚያደርገው ስህተት የተነሳ ሊጎሳቆል ይችላል:: ለምሳሌ፣ በውስጡ ያለውን ያልተቀረጠ የቁጣ እሳት ካለመጠን እንዲነድ የፈቀደ ሰው በዚያው እሳት መቃጠሉ አይቀርም:: ራሱን ከኃጢአት ያልሰበሰበ አገልጋይ እንደማንኛውም ሰው በኃጢአት የሚመጣን በሽታ መለቃቀሙ አይቀርም:: ከእንደዚህ ዓይነቱ መከራ ለመዳን የሚፈልግ አገልጋይ ራሱን ከኃጢያት ሊጠብቅ ይገባዋል:: አንዴ ተሳስቼ አስከፊና መራራ ፍሬ እየበላሁ ነው የሚል ሰው ደግሞ ስላለፈው ኃጢያቱ ንስሃ ይግባ:: እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር የሚል፣ በሽታን የሚፈውስና ኃጢአት የበላውን ዘመን ሁሉ የሚያድስ አምላክ ነው!

*ሐ) ከመልካምነት የሚመጣ መከራ::* ጴጥሮስ ሦስተኛውን የመከራ መንስኤ ያስተዋውቀናል:: እርሱንም፣ *«ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ. . .»* በማለት ይገልጠዋል:: መልካም ማድረግ የሰይጣንንም ሆነ የክፉዎችን ሰዎች ቁጣ ይቀሰቅሳል:: ስለዚህም መልካም አድራጊውን ለማጥመድ ከማድፈጥ አይመለሱም:: ይህ ሁኔታ ግን አገልጋይን ሊበግረው አይገባም:: መከራን ፈርቶ ከእግዚአብሔር ፈቃድና መልካም ከማድረግ መሸሽ ጸጋን ያስጥላል:: ለጌታ ክብር በሚያደርገው መልካም ነገር የተነሳ ጉስቁልናን የሚቀበል አገልጋይ ግን ከክብር ወደ ክብር ያልፋል:: ቃሉም እንደሚል:- *«ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል» (ቁ. 20)::*



## በኢዮብ ማሞ የተጻፉ መጻሕፍት

1. ለአእምሮ የሚመች አገልግሎት
2. ከጥሪ ወደ ተልዕኮ
3. የመንፈስ አንድነት: የጠፋብን እንቁ
4. የመከሲት መቃብር